# C3G

# የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከል ያደረገ መንፈሳዊ ህይወት ዕድገትና የአማኞች ህብረት በ2014-2016 የቤተ ክርስቲያንቷ ስልታዊ ዕቅድ

Prepared by Bible Study department of
Ethiopian Evangelical Church
Dallas Texas

## የመሪዎችና የአስተባባሪዎች ማስጠኛ:

የኢትዮጵውያን ወንጌላዊት ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን የቤት ለቤት ህብረት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በቤተ ክርስቲያናችን ከ2009-2013 የነበረው ስልታዊ እቅድ ጌታ ረድቶን በጥሩ ውጤት ካለቀ በኋላ አሁን ደግሞ ከ2014-2016 የሚቆይ ሌላ ዕቅድ ተዘጋጅቶ መተግበር ከተጀመረ ግማሽ ዓመት አልፎታል። እቅዱም በአጭሩ እንደሚከተለው ተገልጿል።

- **Mission (ተልዕኳችን)**

**Our Mission is to connect people with God, to grow together in Christ, and to care for other, all to God's glory.**
**ተልዕኳችን ለእግዚአብሔር ክብር ሰዎችን ከጌታ እየሱስ ጋር ማገናኘት፣ በክርስቶስ አብረን ማደግ እና ለሌሎች በጎ ማድረግ ነው።**

- **Vision (ራዕያችን)**

**We see a gospel-proclaiming, disciple making, caring, and prospering church.**
**ወንጌልን የምታውጅ፣ ደቀ መዛሙርት የምታፈራ፣ በጎነትን የምታደርግና የምታድግ ቤተክርስቲያን እናያለን**

- **Core Values (እሴቶቻችን)**

- Biblical Teaching
- Worship and Prayer
- Discipleship
- Fellowship
- Connectedness
- Christian Family
- Compassion

- **መጽሐፍ ቅዱሳዊ**
- **አምልኮና ጸሎት**
- **ደቀመዝሙርነት**
- **ኅብረት**
- **ተያያዥነት**
- **ክርስቲያናዊ ቤተሰብ**
- **ርኅራሄ**
- **አገልጋይ መሪነት**

- **Frame Work-የ2014-2016 መሪ ቃላቶች**

  በእቅዱ ቤተ ክርስቲያንቷ ለአራት ነገሮች ትኩረት ሰጥታለች፦ ንዑስ ህብረቶችን እንደገና ማደራጀት፣ለሚሽንና ወንጌል ሥሪጭት፣ለሚቀጥለው ትውልድ እና ለአቅም ግንባታ ይሆናል። Reorganizing small groups, Mission and Outreach, Next Generation, and Capacity Building.

### እንያያዝ ፣ ለማምለክ፣ ለማደግ፣ ለመሄድ

በቤተ ክርስቲያናችን ይህ ጥናት ሲዘጋጅ አጠቃላይ ዓላማው በቤተ ክርስቲያንቷ ተልዕኮ፣ራዕይና እሴቶቿ መሠረት የእያንዳንዳችን አስተዋጽኦ በህይወት በመኖርና በመተግበር ታላቅ ነው። ለዚህም በዕቅዱ መሰረት ህብረትን፣ማደግን፣መሄድንና ማምለክን በተመለከተ በቤት ለቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች እንዲጠናና እንዲተገበር ተዘጋጅቷል። ይህም ጥናት ለብዙ አማኞችም በረከት እንዲሆን ጸሎቷ ነው። መሪውም ይሁን ህብረቱ ጥያቄዎችን ትኩረት እየሰጣችሁ እንብቡት።

**የቤተ ክርስቲያንቷ ትምህርት ክፍል 214-703-0100 (ext 217)**

# የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከል ያደረገ መንፈሳዊ ህይወት ዕድገትና የአማኞች ህብረት
# በ2014-2016 የቤተ ክርስቲያንቷ ስልታዊ ዕቅድ
# Christian Maturity for EEBC Home Fellowship (Bible Study)
# Bible Based Spiritual Growth and Fellowship -
# C3G, EEBC Strategic Planning - (2014-2016)

## ይህ ጥናት ህብረትን፣ማምለክን፣ማደግንና መሄድን በተመለከተ አራት ክፍሎች አሉት።

<u>ክፍል አንድ</u>
ጥናት አንድ
የአማኞች ህብረት መሠረት

**የምንባብ ክፍል፡ የሐዋርያት ሥራ 2፡41-42**

የጥናቱ ዓላማ፡
የክርስትያኖች ህብረት ምን ላይ መመሥረት እንዳለበትና መሠረቱንም ሁል ጊዜ ማጠንከር እንደሚገባን ለማስገንዘብ ነው።

**መግቢያ፡**
ስዎች ለተለያየ አላማ ህብረት መስርተውና ተያይዘው ይኖራሉ። የክርስትያኖች ህብረት ግን እንደሌሎች ህብረቶች አይደለም። በዋነኝነት የቤተሰብ ህብረት ነው። እዚህ ህብረት ውስጥ ለመግባት እያንዳንዱ ሰው ከእግዚብሔር መወለድ አለበት። ይህም የሚሆነው በጌታ በኢየሱስ ሲያምን ነው። በዚህ ጥናት ክርስትያኖች በህብረት አብረው ለመኖርና ለመቀጠል የሚያስፈልጋቸውን ዋና ዋና ነግሮች እናያለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች፡**

**1) ቃሉን የተቀበሉ ሲል የማንን ቃል ነው?** በክፍሉ ይሰብክ የነበረው ማን ነበር?
የጴጥሮስን።

- የሰውን ቃል መቀበል ምን ማለት ነው? ይህን ጥያቄ ከ1ኛ ተሰሎንቄ 2፡13 ጋር በማነጻጸር ተነጋገሩ።
- የሰውን ቃል እንደእግዚአብሔር ቃል አድርጎ መቀበል ማለት፣ ዛሬ አንድ ሰው ሲሰብክ የሚናገረውን ያለምንም ጥያቄ የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለን መቀበል አለብን? ***አይደለም። ይልቁን እንደ ቤርያ ሰዎች መፈተንና መጽሐፍ*** ቅዱስን መመርመር የተናገረው እንደ እግዚአብሔር ***ቃል ነው*** ወይስ ***አይደለም ማለት አለብን።***
- ቃሉን መቀበል ለህብረት ያለው አስተዋጽኦ ምንድን ነው?
  ቃሉን ከሚያምን ሰውና ከማያምን ሰው ጋር ህብረት ማድረግ ልዩነቱ ምንድን ነው?
  በ1ኛዮሐ 1፡3 ከስዎች ጋር ህብረት መሠረታዊው ነገር ምንድን ነው?
- በ1ኛ ተሰሎንቄ 2፡13 መሰረት መጀመሪያ ስታምኑ የሰማችሁትና የተቀበላችሁት/ያመናችሁት ቃል ምንድን ነበር?

2) የአማኝ ጥምቀት ምን ያሳያል? ሮሜ 6፡1~11 በመመልከት መመለስ ይቻላል።
ጥምቀት የአመነ ሰው ከአመነበት ጊዜ ጀምሮ ለጌታ ብቻ ህያው ሆኖ ለመኖር መወሰኑን የሚያሳይ ስርዓት ነው።
3) በሐዋርያት ትምህርት መሰረት መትጋት ምን ምን ያካትታል? ሐዋርያቱ የሚሰጡትን ትምህርት መከታተል።
በአሁን ጊዜ ይህ ለእኛ ምን ማድረግ ነው?
መጽሐፍ ቅዱስን በግል ማጥናት፥ ከሌሎች ቅዱሳን ጋር ሆኖ ማጥናት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ መጽሐፎችን ማንበብ፥ ከአገልጋዮች መማር ወዘተ…
4) በጋራ ማዕድ መቁረስ ሲል የጌታ ራትንም እንዲሁም አብሮ መብላትን ያሳያል።
አብሮ ማዕድ መቁረስ ለመያያዝ ያለው አስተዋፅዖ ምን ይመስላችኋል? ከልምዳችሁ አካፍሉ።
5) የጋራ ጸሎት ለህብረት ያለው አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

ህብረት ሲጠነክር በአንድነት ሆነን የምንጸልየው ጸሎት ፍሬአማ እንደሚሆን፥ በጸሎት ደግሞ ህብረታችችንን ማጠንከር እንችላለን።

6) ከላይ በተዘረዘሩት ነገሮች ሁሉ ይተጉ ነበር ሲል መትጋት ምንድን ነው?

ትጋት ሲጎድል ህብረታችን ምን ሊመስል ይችላል?

ከላይ በተጠቀሱት ላይ ስላላችሁ ትጋት ተወያዩ። የማትተጉባቸውን በግልጽ ተነጋገሩባቸው

7) ከዛሬ ጥናት ምን እንደተማራችሁ አካፍሉ። የጥናቱ ዓላማ ምንድ ነው?

**መደምደምያ:**

እውነተኛና ህያው የሆነ ህብረት እንዲኖረን በህብረቱ ውስጥ ያለውን ሰው ሁሉ በጌታ
በኢየሱስ በማመን፥ በጥምቀት ለጌታ ብቻ ለመኖር በመወሰን እንዲሁም በጌታ እራትና በጸሎት ከቅዱሳን ሁሉ ጋር አብሮ በመትጋት መኖር እንዲችል ግድ ማለት አለብን።

**ጥናት ሁለት**
**የአንድ አካል ብልቶች**

የምንባብ ክፍል: እያንዳንዱ ጥያቄ ውስጥ ይገኛል።

**የጥናቱ ዓላማ:**

እርስ በእርሳችን የአንድ አካል ብልቶች መሆናችንን አውቀን በፍቅር በመያያዝ እንደ አንድ አካል አብረን ማደግ እንድንችል ለማሳሰብ ነው።

**መግቢያ:**

አንድ አካል ውስጥ ብዙ የተለያዩ ብልቶች እንዳሉና እነዚህም ብልቶች የየራሳቸው ሥራ እንዳላቸው፥ እንዲሁም ሁሉም ተያይዘው አንዱ በአንዱ እየተጠቀመ አካሉን እንደሚያሳድግ፥ እንዲሁ በክርስቶስ አካል ውስጥ ያለን ሁላችን የተለያየ ጸጋና ሥራ ያለን ነገር ግን ሁላችን ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ለማደግ በፍቅር መተሣሠርና አንዳችን በአንዳንችን መጠቀም አለብን። ይህ ሲሆን ብቻን ነው ህብረታችን ህይወት ያለውና የሚያድግ የሚሆነው።

የመወያያ ጥያቄዎች:

1) የአንዱ የክርስቶስ የአካሉ ብልቶች ነን

ሀ) በሮሜ 12፡4-8 መሠረት

- እኛን በምን ይመስለናል?
- ይህ ለእርስ በርሳችን ግንኙነት ምን ትርጉም አለው?
- በእርግጥ ሌሎች ቅዱሳን ያስፈልጉኛል?
- ያለእነርሱ በክርስትና ህይወቴ ማደግ ይቻላል ወይስ አይቻልም? እያብራራችሁ ተነጋገሩ
- ያለ እነርሱ በክርስትና ህይወቴ ማደግ ይቻላል ወይስ አይቻልም? እያብራራችሁ ተነጋገሩ።
- ስለዚህ ምን እናድርግ?

መልስ: እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን

አንድ ሰው አንድ ብልት ብቻ ነው። ለምሳሌ፥ አንድ ሰው እጅ ብቻ ሊሆን ይችላል እንጂ የሰውነትን አካል ሁሉ መሆን አይችልም፥ ስለዚህ እጅ የሆነው ሰው እግር ያስፈልገዋል፥ ይህም ማለት አንዱ ለጌታ ስራ በተለየ ሁኔታ በልግስና መስጠት ሲችል፥ ሌላው ደግሞ ለጌታ ስራ እግር ሆኖ እጅ የሆነው ወደማይሄድበት ሊሄድ ይችላል። ሁላችንም መሄድ አንችልም። ሁላችንም እኩል መስጠት አንችልም።

**<u>ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በሚቀጥለው ቀን መወያየት ትችላላችሁ</u>**

ለ) በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፡22~26 ደካማ የሆኑትን ወይም በተለያየ ምክንያት የምናፍርባቸው የክርስቶስ አካል ብልቶች ካሉ ምን ማድረግ አለብን?

ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው እነዚህ?

***በባህርያቸው ወይም በማንኛውም ጉዳይ እንደ ክርስትያን የማይኖሩ ከዚህም የተነሳ የምናፍርባቸው ሰዎች ከነዚህ መካከል ናቸው። እነዚህን በደንብ ልንንከባከባቸው፥ልናከብራቸው፥ ፍቅር ልናሳያቸው ይገባል።***

ሐ) በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡33 የጌታን እራት ስንወስድ እርስ በእርሳችሁ ተጠባበቁ፥ የተራብ ካለ ቤቱ ይብላ የሚለው ለምን ይመስልሃል?

እንደ አንድ አካል ራሳችንን እንድናይ ነው። የጌታ እራት በግል ከጌታ ጋር የገባነውን ኪዳን የምናድስበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን፥ ከእርሱ ጋር ህብረት ካላቸው ሁሉ ጋር ህብረታችንን የምናጠናክርበት ጊዜ መሆን አለበት። ለዚህም እንዲረዳ ቢቻል የጌታ እራት የምንወስድ እለት የምንችል ሰዎች በአንድነት ማዕድ በመቁረስ ስለጌታ ሞትና ትንሳኤ የምንነጋገርበትና የምንጸልይበት ሁኔታ ብንፈጥር መልካም ሊሆን ይችላል። ይህ ግን ህግ ሊሆን አይገባውም።

2) በቆላስያስ 3፡12-15 መሠረት የክርስቶስ አካል ብልቶችን በአንድነት የሚያያይዝ ምንድን ነው? የተለያየ ጸጋና ሥራ ያለን ብልቶች መሆናችን ሊያለያየን አይገባም። ልዩነታችንን ግን በፍቅር አካሉን ለመገንባት ወደሚያስችል አንድነት ልንለውጠው ይገባል።

ሀ) በዮሐንስ 13፡34፤ 15፡12 እና 17 ስለ እርስ በርስ ፍቅር ምን እናነባለን? የጌታ ኢየሱስ ትዕዛዝ መሆኑስ ምን ያመለክታል?

<u>***ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በሚቀጥለው ቀን መወያየት ትችላላችሁ***</u>

ለ) በ1ኛ ዮሐንስ 3፡11 አማኞች ከመጀመርያ አንስቶ የሰሙት መልዕክት ምንድን ነው? ስለ እርስ በርስ ፍቅር።

ከላይ ትዕዛዝ እንደ ነበር አይተናል፥ አሁን መልዕክት ያለው ለምንድን ነው?

ይህ የእኛን ድርሻ ያሳያል። ጌታ ያዘዘውን እኛ ለሰዎች ከመጀመርያው ጀምሮ ልናስተላልፍ የሚገባን መልዕክት ነው።

ከመጀመርያው ሲል ጌታን ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ ማለት ነው። ከዚህ ምን እንማራለን?

ሐ) በ1ኛ ዮሐንስ 3፡23 ኢየሱስ ያዘዛቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?

ኢየሱስን ማመንና እርስ በእርስ መዋደድ።

መዋደድን ክርስቶስን ከማመን ጋር ማያያዙ ምን ያሳያል?

***ሰው ኢየሱስን እንዳመነ ሌላው ሊነገረው የሚገባ እውነት ስለ እርስ በርስ ፍቅር ነው።***

መ) በ1ኛ ዮሐንስ 4፡7 መሠረት እርስ በርሳችን እንድንዋደድ የምንችለው እንዴት ነው?

1) ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለሚመጣ

2) እኛ ደግሞ ከእግዚአብሔር ስለተወለድን። ስለዚህ መውደድ የሚያስችል ዘር በውስጣችን መኖሩን ልናውቅ ይገባል።

ሠ) ፍቅር ከእግዚአብሔር ዘንድ ቢመጣም፥ እኛም ከእርሱ የተወለድን ስለሆንን ማፍቀር የምንችልበት ዘር በውስጣችን ቢኖርም፥ በዕብራውያን 10፡24 መሠረት ምን ማድረግ አለብን? ይህን ማድረግ ለምን አስፈለገ?

***እርስ በእርስ መተያየት። የአንድ አካል የተለያዩ ብልቶች ስለሆንን፥ እንደብልት አንዳችን በአንዳችን ላይ ስለምንደገፍ ነው።***

ረ) በ1ኛ ተሰሎንቄ 3፡12 ጳውሎስ ስለ እርስ በእርሳቸው ፍቅር የሚለውን ሁለት ነገሮች ጥቀሱና ተወያይ።

1) ለሁሉም የሚሆን

2) ያብዛ ይጨምርም ብሎ ይጸልያል።

ለሁሉም የሚሆን ማለቱ ስለ እርስ በእርስ ፍቅር ምን ያስተምራል?

***የፈለግነውን እየመረጥን ሳይሆን ለወንድሞች ሁሉ አንድ አይነት ፍቅር ማሳየት እንዳለብን ያሳያል።***

መጸለዩ ምን ያሳያል?

***ማፍቀር የሚያስችለን ፍቅር በውስጣችን ቢኖርም፥ እርስ በርስም እየተያየን ብንበረታታም፥ የጌታን እርዳታ በመፈለግ መጸለይ እንዳለብንም ያሳያል።***

ሰ) በሮሜ 13፡8 የተፈቀደው የምን እዳ ብቻ ነው? የፍቅር ዕዳ።

የፍቅር እዳ ማለት ምን ማለት ነው? ለምን ተፈቀደ?

***ሰዎችን ሁሉ መውደድ ስላለብን፥ ሁሌ ልንወዳቸው የሚገቡ ስላሉ። የተፈቀደው፡ የምንወዳቸው ሰዎች ቢኖሩም፥ ፍቅራችንን የሚፈልጉ ሌሎች ሰዎች ስላሉ ነው። ደግሞም በአንዴ ሁሉንም መውደድ ሊያስቸግረን ስለሚችል። ከእዳ የምንወጣው በሂደት መሆኑን ያሳያል።***

ሸ) የጥናቱን ዓላማና የተማራችሁትን ነገር ተነጋገሩ? አማኞችንና ሌሎችንም እንጠላለን? አሁን ራስን ማየት አለብን። ምን ይሻላል?

**መደምደምያ፡**

ሁላችንም ላለንበት ህብረት የሚጠቅም ድርሻ ስላለን፥ በፍቅር ተያይዘን አንዳችን

ባንዳችን እየተጠቃቀምን ማደግ አለብን።

**ጥናት ሦስት**

**የእርስ በእርስ ክርስትና**

**ክፍል አንድ**

የምንባብ ክፍል፡ እያንዳንዱ ጥያቄ ውስጥ ይገኛል።

የጥናቱ ዓላማ፡ እርስ በእርሳችን ልናደርጋቸውና በተቃራኒውም ልናስወግዳቸው የሚገቡንን ነገሮች ለማሳወቅ።

መግቢያ፡

አካል ተያይዞ ማደግ እንዲችል፥ እያንዳንዱ ብልት ስራውን መስራት አለበት።እንዲሁም ጤነኛ አካል እንዲኖር ጤነኛ ብልቶች መኖር አለባቸው። አንዱ ብልት ሥራውን በደንብ መሥራት ካልቻለ ወይም ጤነኛ ካልሆነ፥ አካሉ ጤነኛ አይሆንም። እንዲሁ አንዳችን ላንዳችን የተሰጠንን በመስጠት አካሉን ማሳደግ አለብን። እያንዳንዳችን ጤነኛ መሆን እንድንችል ልንተጋገዝ ይገባናል።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡***

1) በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡11

- ከመግቢያ ጽሑፍ ምን ተማራችሁ?
- በአንድ ልብ ሁኑ ሲል ምን ማለት ነው?
- በአንድ ልብ መሆን ይቻላል?
- በሮሜ 15፡6 ላይ በአንድ ልብ መሆን የሚያስፈልገን ትልቁና ዋነኛው አላማ ምንድን ነው? ***በአንድ አፍ እግዚአብሔርን ማክበር እንድንችል።***

2) በሮሜ 12፡16

- በአንድ ሃሳብ ተስማሙ ሲል ምን ማለቱ ነው?
- በምናስበው ሁሉ አንድ ሃሳብ አስቡ ነው? ካልሆነስ? መልስ አይደለም ነገር ግን ለአንድ ግብ፥ ለአንድ አላማ በማሰብ ኑሩ ማለቱ ነው።

3) በዕብራውያን 3፡12-13 በማንበብ የሚመለሱ ጥያቄዎች

- በመካከላችን (በአንዳችንም ልብ ውስጥ) አለማመንና ሃጢያት እንዳይገኝ ደግሞም ሃጢያትም እያታለለ እልከኛ እንዳያደርገን እርስ በርሳችን ልናደርግ የታዘዝነው ምንድን ነው?
- ተጠንቀቁ እና ተመካከሩ (በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ተጽናኑ)። እንዴት ነው የምንጠነቀቀው?
- ሃጢያት የሚያታልለውን ሰው እንዴት መምከር/ማጽናናት ይቻላል?
- በመጠንቀቅና በመምከር/ማጽናናት ማደግ እንዴት እንችላለን?

4) በቆላስያስ 3፡16 በተለይ በጥበብ ሁሉ ተማማሩ፤ ተገሣሡ ሲል፤

- በጥበብ እርስ በእርስ መማማር ምን ማለት ነው?
- ያለመማማርና ያለመገሣሥጽ በህብረት ማደግ ይቻላል?

- ካልተቻለ በእነዚህ በሁለቱ ለማደግ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?
- በተለይ በግል ማድረግ ያለባችሁን አካፍሉ።
- በጥበብ ማስተማርና መገሥጽ ምን ይመስላል? በዚህ ነገር ያለን ድካም ምንድ ነው?

***የራስን ድካም ምሳሌ በማድረግ፥በጥያቄ መልክ በማቅረብ፥ የሚነበብ ነገር በመስጠት፥ እዚሁ በቆላስያስ 3፡16 እና በኤፌሶን 5፡19 በመዝሙር፥ በቅኔ፥ በመንፈሳዊ ዜማ መነጋገርና ወዘት ያካትታል።***

<u>ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በሚቀጥለው ቀን መወያየት ትችላላችሁ</u>

5) በኤፌሶን 4፡1-3 (ቁ.2 በአዲሱ መደበኛ ትርጉም)

- የተዘረዘሩ አራት ለህብረታችንን ወሳኝ የሆኑ ባህርያትን ትርጉማቸውንና ለመያያዛችን ያላቸውን አስተዋፅዖ ተወያዩ።
- ፍጹም ትሑታንና (ሃይል የማይጠቀም ሰው መሆን) ገሮች ሁኑ፤እርስ በርሳችሁም በፍቅር እየተቻቻላችሁ ትዕግሥተኞች ሁኑ። ትሑት መሆንን የምናሳይባቸው መንገዶች ምን ምንድን ናቸው?
- መቻቻል ማለት ምን ማለት ነው? ለምንስ አስፈለገ?

6) በያዕቆብ 5፡16 በማንበብ ተወያዩ

- እንድናደርጋቸው የታዘዝናቸው ምንድን ናቸው?
- በእነዚህ ላይ ያላችሁን ልምምድ አካፍሉ። እንዴት ነው በእነዚህ ማደግ የምንችለው?

7) በኤፌሶን 5፡21 አንዳችሁ ለሌላው በጌታ ፍርሃት ተገዙ ሲል በጌታ ፍርሃት ለእርስ በርስ መገዛት ምን ምን ያካትታል?

8) በሮሜ 12፡10 ተከባበሩ ሲል እርስ በእርስ መከባበር ምን ያካትታል? ወንድሜን እንዳከብረው ከእርሱ ምን ያስፈልጋል? ምንም።

9) በ1ኛ ጴጥሮስ 5፡14፤ በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡12፤ በ1ኛ ቆሮንቶስ 16፡20፤ በሮሜ 16፡16 የታዘዝነው ምንድን ነው? ይህ ለህብረታችንና ለመያያዛችን የሚሰጠው አስተዋጽኦ ምንድን ነው?

10) የዚህ ጥናት ዋና ዓላማው ምንድ ነው? በአጠቃላይ ከጥናቱ ምን ተማርን?

መደምደምያ:

አንድ አካል ስለሆንን፥ እያንዳንዳችን ስለራሳችንም ስለሌላውም መንፈሳዊ ጤንነት
ግድ ሊለን ይገባል።

**ጥናት አራት**
**የእርስ በእርስ ክርስትና**
**ክፍል ሁለት**

የምንባብ ክፍል፡ እያንዳንዱ ጥያቄ ውስጥ ይገኛል።

**የጥናቱ ዓላማ፡**
እርስ በእርሳችን ልናደርጋቸውና በተቃራኒውም ልናስወግዳቸው የሚገቡንን ነገሮች ለማሳወቅ።

***መግቢያ፡***
አካል መያያዝ ብቻ ሳይሆን ማደግ አለበት። ለማደግ ደግሞ መያያዙ ብቻ ሳይሆን፥ እያንዳንዱ ብልት ሥራውን መሥራትና አንዱ በሌላው ብልት መጠቀም ያስፈልጋል። ስለዚህ በፍቅር ተያይዘን፥ አንዳችን ላንዳችን የተሰጠንን በመስጠት አካሉን ማሳደግ አለብን።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡***
1) በያዕቆብ 4፡11 ሲነበብ
- በወንድም ላይ ስለመፍረድ ምን እንማራለን?
- ለምን መፍረድ ተከለከልን?

***አንድ ብቻ ፈራጅ ስላለ። የእኛ ድርሻ ወንድምን መርዳት፥ ስለእርሱ በፈራጁ ፊት መማለድ ነው።***

2) በሮሜ 14፡1-3 እና 13 በማንበብ ተወያዩ
- ማን ነው መፍረድ የሌለበት?

በተለይ ብርቱ የሆነው ግን ሁላችንም በዚህ ፈንታ ቁጥር 19 ምን እንድናደርግ ያዘናል? "ስላም የሚቆምበትን እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን እንከተል።"
- 'ስላምን ለመፈለግና ሁላችንም የምንታነጽበትን ለመፈለግ' ከእያንዳንዳችን የሚፈልገው ምን ምንድን ነው?
- ሰላምን በማምጣት ሂደት አንደኛው ወገን የደከመ ወይም ትኩረት የማይሰጥ ቢሆን ምን ማድረግ እንችላለን?

3) በኤፌሶን 4፡31እና 32 መሰረት
- ከመካከላችን ሊወገዱ የሚገባቸው ክፉ ባህርያት ምን ምንድን ናቸው?

በመያያዛችን ላይ ምን ችግር ይፈጥራሉ? በዚህ ፈንታ የታዘዝነው ምንድን ነው?
- ሦስት ድርጊቶችን ጥቀሱና ከተከለከሉት ባህርያት ጋር እያነጻጸራችሁ ተወያዩ:: ለመያያዛችን የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ ተነጋገሩባቸው።

4) በፊልጵስዩስ 2፡1-3 መሰረት
- ልናደርግ የተከለከልነው ምንድን ነው?

ለወገኔ ይጠቅማል ማለትን (በአዲሱ መደበኛ ትርጉም በራስ ወዳድነት ነገሮችን ማድረግ) እና ከንቱ ውዳሴ (ምስጋና ፈልገን ወይም ስማችንን ለማስጠራት ብለን ማድረግ ተከልክለናል)።
- ለምንስ ተከለከልን?

ቅዱሳንን ሁሉ እንድንወድ እንጂ ወገን ፈጥረን ለምንቀርባቸው ሰዎች ብቻ እያሰብን መኖር አንድነትን ያፈርሳል። ራስ ወዳድ መሆን ማለት ለግላችንም ለምንቀርባቸውም ሰዎች ብቻ ማሰብ ነው።
- አድርጉ የተባለውስ ምንድን ነው? ባልጀራው ከእርሱ እንደሚሻል ይቁጠር።
- ይህ ምን ማለት ነው?

የወንድሜ ችግር ይብሳል ብሎ ቅድሚያ ለሌላው መስጠት ነው፤ አንተ ትብስ፥ አንቺ ትብሽ ማለት ነው።

**ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በሚቀጥለው ቀን መወያየት ትችላላችሁ**

5) በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡15 መሰረት

- የተከለከልነውና እንድናደርግ የታዘዝነውን በማነጻጸር ተወያዩበት።
- ለህብረታችን ያላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ አስተዋጽኦ ተነጋገሩ።

6) በማቴ 24፡10 ውስጥ የተጠቀሱ

- ሁለት የህብረት እንቅፋቶች ምን ምንድን ናቸው? ዕንቅፋት የሚሆኑት እንዴት ነው? ሁለቱስ እንዴት ይገናኛሉ። መጥላት እና አሳልፎ መስጠት/መካድ።
- ጠላን የሚባለው ምን ስናደርግ ነው?
- አሳልፎ መስጠት ምን ማለት ነው?
- ዛሬ እንዴት ነው አንድ ወንድም ሌላውን አሳልፎ ሊሰጥ የሚችለው?

7) በቆላስያስ 3፡9 እና በኤፌሶን 4፡25 በማንበብ

- ከህብረት ሊወገድ የሚገባ ነገር ምንድን ነው? በህረት ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል?

8) በገላትያ 5፡15

- እርስ በእርሳችን ልናደርገው የማይገባ ነገር ምንድን ነው? ካላስወገድነውስ የሚከተለው ችግር ምንድን ነው?
- በእርግጥ እንዲህ አይነት ችግር በእኛ መካከል ሊፈጠር ይችላል? መነሻዎቹ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
  አትነካከሱ፡ በንግግር መጎዳዳት፥ ስም ማጥፋት
  አትጠፋፉ፡

9) በገላትያ 5፡26 መሠረት ወደ መነካከስ የሚያደርሱን ምን ምንድን ናቸው?

1) አታስቆጡ 2) አትቅኑ 3) አትታበዩ

10) ሌሎች የህብረት ዕንቅፋቶች የምትሉአችውን ተወያዩባቸው

11) በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡18 እርስ በርሳችን የምንጽናናበት ቃል ምንድን ነው?

ጌታ መጥቶ ይወስደናል ከእርሱም ጋር እንሆናለ።

12) የዚህ ጥናት ዋና ዓላማው ምንድ ነው? ከጥናቱ ምን ተማርን?

***መደምደምያ***

ጌታ እስኪመጣ ድረስ እርስ በእርስ በመተጋገዝ ልንኖር እንጂ አንዱ የአንዱ
ፈራጅ ወይም እንቅፋት ሊሆን አይገባም።

**<u>ክፍል ሁለት</u>**
**አምልኮ**
**ጥናት አንድ**

## የአምልኮ ምንነት

**ለአስጥኚው፡- እባክዎን ለዚህ ጥናት ብዙ ዝግጅት ያድርጉ**

**ዓላማ፡-**

የመጽሐፍ ቅዱሳዊ አምልኮን ትርጉም በወጉ መረዳትንና በአግባቡ ማከናወንን ለማስተማር::

**መግቢያ**

በጥንቱ አንግሎ-ሳክሶን የእንግሊዝኛ ቋንቋ "አምልኮ" (worship) የሁለት ቃላት ቅንጅት (woerth & scipe) ሲሆን መንፈሳዊ ፍቺውም **<u>ለማንነቱ የሚገባውን ክብር መስጠት</u>**ማለት ነው።ቃሉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይኖርም አምልኮ በእብራይስጡ ሻካ፤ በግሪኩ ፕሮስኩኔኦ ሲባል ትርጓሜውም ለበላይህ ባለሥልጣን ለጥ ብሎ እጅ በመንሳት የሚገባውን ክብር መስጠት ማለት ነው። አምልኮ ኃይልና ባለጠግነት፣ ጥበብና ብርታት፣ ክብርና ሞገስ፣ ምስጋናም ሊቀበል የሚገባውን እግዚአብሔርን በትሁት መንፈስ እንደ ፈቃዱ እያገለገሉ ለታላቅነቱ የሚገባውን መልስ መስጠት ነው። (1ዜና:- 16:28-29 ፤ መዝ:- 29:1-2 ፤ ራዕ:- 4:10-11፤ 5:11-14):: ሆኖም ግን የመዝገበ ቃላት ትርጉም ብቻ አምልኮን በወጉ አይገልጸውም። አመርቂ ትርጉም የሚኖረው በዐውደ ምንባቡ መሰረት የተረጎምን እንደሆነ ነው።

**በዘወትር ዕይታ**

አምልኮ:-

- ለእግዚአብሔር/የምስጋናን መስዋዕት/የከንፈሮችን ፍሬ ማቅረብ (ዕብ:-13:15-16)
- ለምህረቱና ለቸርነቱ ምላሽ መስጠት (መዝ፡-100: 4-5)
- ለብቻው እውቅናን መስጠት (ነህ:- 9:6)
- በፊቱ ራስን ማዋረድ (መዝ:- 95-6-7)
- በመንገዱ እግዚአብሔርን መምሰል (መዝ:-96:9)
- ራስን ለእግዚአብሔር ማቅረብ (ሮሜ:- 11:35-12:1) ሲሆንድርጊቱም በእውነትና በመንፈስ ሊሆን ያስፈልጋል።

**ዕውን አምልኮ**

ሁሉ ነገር ከእርሱ፤ በርሱና ለእርሱ ስለሆነ ዓምልኮ ዕውን የሚሆነውም:-

1. እግዚአብሔር በጸጋው ለኛ ያለውን መልካሙን ዓላማውን፤ ዕቅዱንና ፈቃዱን ሲገልጽልን
2. ከእርሱ ጋር በክርስቶስ በኩል የተገኘና በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸ መልካም የግል ሕብረት ሲኖረን
3. በደስታ የተሞላ የማክበር፤ የማንገስ፤ በትህትና ራስን የማስገዛትና የመታዘዝ ሕይወት ሲኖረን ነው።

ስለሆነም በተለምዷዊ ሥርዓት ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት ስለማይቻል በፍጹም ልባዊ መሰጠት እግዚአብሔርን ለማምለክ አስቀድሞ እርሱን ማወቅ (በባሕሪው እርሱን መምሰል) ያስፈልጋል።

**የእግዚአብሔር ባህሪያት**

1. ሁሉንአወቅ (Omniscient) - ኢዮ:- 37:16 ፤ መዝ:- 147:5 ፤ ኢሳ:- 40:28
2. ሁሉንቻይ (Omnipotent) - ዘፍ:- 18:14 ፤ ኢዮ:- 42:2

3. በሁሉምቦታ የሚገኝ (Omnipresent) - ምሳ:- 15:3፤ ኤር:- 23:23-24
4. ንጉሥ-ነገስታት/እንዳሻው(Sovereign) - ኤፌ:- 1:11 መዝ:- 115:3 ፤ ሮሜ:- 11:33-34
5. ቅዱስ (Holy) - መዝ:- 99:9, ዕም:- 1:13
6. ጻድቅ (Righteous) - ዕዝ:- 9:15, መዝ:- 116:5 ፤ ኤር:- 12:1 ፤ 1ዮሐ:- 1:9
7. በራሱ ነዋሪ/ያለና የሚኖር (Self-Existent) - መዝ:- 90:2፤ራዕ;-4:10፤ ዘጸ:- 3:14
8. አይለወጤ (Immutable) - ሚል:- 3:6
9. ፍቅር (Love) - 1ዮሐ:- 4, ዮሐ:- 3:16
10. መሐሪ (Merciful) - ዘዳ:- 4:3 ፤ መዝ:- 103:8 ፤ኤር:- 2:4፤ ሮሜ:- 5:8

በዘፀ:- 34:5-9 እግዚአብሔር ስለ ራሱ እንደዚህ ሲል አውጇል:-

"እግዚአብሔርም በፊቱ አልፎ እግዚአብሔር፥ እግዚአብሔር መሐሪ፥ ሞገስ ያለው፥ ታጋሽም፥ ባለብዙ ቸርነትና እውነት፥ እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ፥ አበሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል፥ በደለኛውንም ከቶ የማያነጻ፥ የአባቶችንም ኃጢአት በልጆች እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድም በልጅ ልጆች የሚያመጣ አምላክ ነው::" እንግዲህ አምልኮ ተፈጥሮአዊ ማንነታችንን ለእግዚአብሔር መስጠት ነው። አምልኮ ህሊናን ለቅድስና ማነሳሳት፤ አዕምሮን በእርሱ እውነት መመገብ፤ አመለካከትን በውበቱ ማንጻት፤ ልብን ለፍቅሩ ማስማረክና ፈቃድን ለዓላማው ማስገዛት ነው።

ፍጹም የሆነ ሕይወት ላይኖረን ይችላል፤ ወሳኙ ግን የልባችን ዝንባሌ ነው። ዳዊት ያለ ኃጢዓት አልነበረም፤ እግዚአብሔር ግን እንደ ልቤ የሆነልኝ ብሎታ; (የሐዋ፥፡ 13:22) ገና ተሰርተን ያላለቅን ብንሆንም ከእግዚአብሔር ጋር ኅባሬያዊ ተግባቦት (መናበብ) ሊኖረን ይገባል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በመግቢያው መሰረት የአምልኮን ትርጉም ያብራሩ
2. በራዕይ ያሉት ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች አክሊላቸውን የማውለቃቸው ሁኔታ ምንን ያሳያል?

ራዕ:- 4:10-11፤ 5:11-14

3. እግዚአብሔር ዓላማውን፤ ዕቅዱንና ፈቃዱን ሳይገልጽልንስራውን መስራትይቻላል? (ዮሐ:- 15:4)
4. ተከታዮቹን አባባሎች በማብራራት ተወያዩ

ሀ)የከንፈሮችን ፍሬ ማቅረብ (ዕብ:-13:15-16

ለ) ለምህረቱና ለቸርነቱ ምላሽ መስጠት (መዝ፡-100: 4-5)

ሐ) ለብቻው እውቅናን መስጠት (ነህ:- 9:6

መ) በፊቱ ራስን ማዋረድ (መዝ:- 95-6-7)

ሠ) በመንገዱ እግዚአብሔርን መምሰል (መዝ:-96:9)

ረ) ራስን ለእግዚአብሔር ማቅረብ (ሮሜ:- 11:35-12:1)

<u>**ጊዜ ካልበቃችሁ ከዚህ በታች ያለውን በሚቀጥለው ቀን አጥኑ**</u>

5. ለአምልኮ የአምላካችንን ባህሪያት ማወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው። የምናመልከውን የአምላካችንን የእግዚአብሔርን ባሕሪያት ያብራሩ (ይህን ማወቅ ለአምልኮ ምን ይጨምራል)

ሀ) ሁሉን አወቅነቱን መዝ:- 147:5 ፤ ኢሳ:- 40:28

ለ) ሁሉን ቻይነቱን ዘፍ:- 18:14 ፤ ኢዮ:- 42:2

ሐ) በሁሉም ቦታ የሚገኝ መሆኑን ምሳ:- 15:3፤ ኤር:- 23:23-24

መ) አይለወጤነቱን  ሚል:- 3:6

ሠ) ቅድስናውን መዝ:- 99:9, ዕም:- 1:13

ረ) ጻድቅነቱን  ዕዝ:- 9:15, መዝ:- 116:5 ፤ ኤር:- 12:1 ፤ 1ዮሐ:- 1:9

ሸ) ንጉሰ ነገስትነቱን    ኤፌ:- 1:11 መዝ:- 115:3 ፤ ሮሜ:- 11:33-34

ቀ) ፍቅር መሆኑን    1ዮሐ:- 4, ዮሐ:- 3:16

በ) መሐሪነቱን ዘዳ:- 4:3 ፤ መዝ:- 103:8 ፤ ኤር:- 2:4፤ ሮሜ:- 5:8

ተ) ያለና የሚኖር ዘጸ 3፡14

6. እግዚአብሔር ስለ ራሱ በዘፀ:- 34:5-9 የተናገረውን ያብራሩ::
7. ዳዊት ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆነለት እንዴት ነበር? ይህስ ስለ አምልኮ ምን ይናገረናል?
8. ዓምልኮ ዕውን የሚሆነው እንዴት ነው ?
9. ከዛሬው ጥናት ያገኙትን ትምህርት ያካፍሉ::

**መደምደምያ:-**

አምልኮ ህሊናን ለቅድስና ማነሳሳት፤ አዕምሮን በእርሱ እውነት መመገብ፤ አመለካከትን በውበቱ ማንጻት፤ ልብን ለፍቅሩ ማስማረክና ፈቃድን ለዓላማው ማስገዛት ነው። ፍጹም የሆነ ሕይወት ላይኖረን ይችላል፤ ወሳኙ ግን የልባችን ዝንባሌ ነው።

## ጥናት ሁለት

## የአምልኮ ታሪካዊ ዳራ

**ዓላማ:-** መመሪያችን ከሆነው ሙሉ የእግዚአብሔር ቃል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ አምልኮን ለይተን እንድናውቅ መንደርደሪያ ለመስጠት::

**መግቢያ:-**

አምልኮን በመጽሐፍ ቅዱስ ዕይታ ስናጤነው ታሪካዊ ዳራ ያለውና የሰው ልጅ እግዚአብሔር በገለጠለት መጠን በግልም ይሁን በሕብረት፤ በተለያዬ ቦታም ይሁን በተወሰነ ስፍራ አምላኩን ከፍ ከፍ የሚያደርግበት ፍጡራዊ ምላሽ ሆኖ እናገኘዋለን። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንኑ ሃሳብ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ ያሳዩናል። በመቀጠል ታሪካዊ ዳራውን ከሙሴ በፊት፤ በዘመነ ሙሴ፤ በሙከራብ አምልኮ ወቅት፤ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያንና በዘመነ ጳውሎስ በአጭሩ እንመለከታለን።

### ሀ. አምልኮ ከሙሴ በፊት

መጽሐፍ ቅዱሳችን ስንመረምር ከሙሴ በፊት የነበሩ ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ምሪት በመቀበልም ሆነ በራሳቸው መነሳሳት እግዚአብሔርን በልዩ ልዩ መንገድ ያመልኩ እንደ ነበር እናስተውላለን። ርቀን ሳንሄድ ዘፍ 4 ላይ አቤልና ቃዔል መስዋዕት አቅርበው እግዚአብሔርን እንዳመለኩ እናስተውላለን። በመቀጠልም በዘፍ 8 ና 9 ላይ ኖህ ለእግዚአብሔር መልካም መዓዛ ሽታ ያለውን መስዋዕት በማቅረቡ እግዚአብሔር እርሱንና ቤተሰቡን እንደባረከ እንመለከታለን። በመቀጠልም አብራሃም በሴኬም፤ በቤቴል፤ በኄብሮንና በሞሪያ ተራራ ላይ መሰዋዕት በማቅረብ እግዚአብሔርን እንዳመለከእናያለን። ይስሐቅም በቤርሳቤህ መሰዊያ እንደሰራና እንደጸለዬ እናያለን። ያዕቆብም በቤቴል የድንጋይ ሐውልት በማቆምና ዘይት በማፍሰስ እግዚአብሔርን እንዳመለከ እናስተውላለን። መሰዊያንም በቤቴልና በሴኬም አቁሞ እንዳ መለከ እናያለን። እንግዲህ በጋራ የምንረዳው እነዚህ ግለሰቦች፥፡

1. አንዳቸውም ካህን እንዳልነበራቸውና ራሳቸው የየግላቸውን መሰዊያ በማቆም እንስሳትን ሰውተው እንዳመለኩ የቤቱ መሪ እንደ የሐይማኖቱም መሪ እንነበረ
2. አባቶች ስላከናወኑት አምልኮ ከእግዚአብሔር የተሰጠ በዙ መመሪያ እንዳልነበረ፤ ልዩ የአምልኮ ቀንም ሆነ ወቅት እንዳልተደነገገ ሆኖም እግዚአብሔርን ብቻ በፈለጉት ቦታ፤ በፈለጉት ዓይነትና ጊዜ እንዳመለኩ
3. ብዙም የአሰራር መንገድ እንዳልነበረ። ሆኖም ወይን ወይም ዘይት መሰዊያው ላይ በማፍሰስ፤ እነሰሳውን ሙሉ በሙሉ በማቃጠል፤ ወይም በመጥበስና ከፊሉን በመበላት አምልኮን ያካሂዱ ነበር።

ለአቤል፤ ለኖህ፤ ለአብርሐም፤ ለያዕቅብ ጊዜ ስፍራና መመሪያ አምልኮአቸውን አይወስንም ነበር። ለሁሉም ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ የሚል ነበር። እግዚአብሔር ስለሚገባው መቶ ከሙቶ ብቻውን መመለከን ይሻ ነበረ፤ አስፈላጊውም ይህ ነበር።

### ለ. ሙሴና የማደሪያ ድንኳን

በዘመነ ሙሴ አምልኮ ቀለል ካለ የአፈጻጸም ሂደት ወደ ዝርዝር መመሪያና መዋቅር አዘል አሰራር ተለወጠ። እግዚአብሔር አምላክ በጥልቀትና በዝርዝር፥

1. መስዋዕት መቼ መደረግ እንዳለበት
2. እንዴት መደረግ እንዳለበት
3. የት መደረግ እንዳለበትና

4. ማን ማድረግ እንዳለበት ደነገገ።

ከዚህም የተነሳ አምልኮ መደበኛና ደንብ አዘል ሆነ። እናም በሙሴ ሕግ የተቀደሱ ቦታዎች፤ የተቀደሱ ሰዎች፤ የተቀደሱ እንስሳት፤ የተቀደሱ ኃይማኖታዊ ሥርዓታትና የተቀደሱ ዕለታት ነበሩ። የማደሪያውን ድንኳን ብንወስድ አደባባዩ ቅዱስ፤ ቅድስተ ክፍሉ በጣም ቅዱስ፤ ቅድስተ ቅዱሳኑ እጅግ በጣም ቅዱስ እንደ ነበሩ እንገነዘባለን። ወደ እግዚአብሔርንም በተፈለገው ጊዜ አይቀረብም ነበር። ስግደተ አምልኮው በተቀደሰሰው፤ በተቀደሰ ጊዜ፤ ወደ ተቀደሰው ስፍራብ ተቀደሰ ሥርዓተ አፈጻጸም መሆን ነበረበት። እንግዲህ የማደሪያው ድንኳን የእግዚአብሔርን ቅድስና በግልጽ የሚያሳይ ነበር። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ከሕዝቡ የራቀ አልነበረም። በማደሪያው ድንኳን በሕዝቡ ሰፈር ነበር።

በጥንቷ እስራዔል በማደሪያው ድንኳን በእግዚአብሔር ጥሪ ሊያመልኩና ሊያስመልኩ የተቀደሱ (የተለዩ) ሌዋውያን የሚባሉ ሰዎች ነበሩ። የተቀደሱ እንስሳትና እጽዋት ነበሩ። የበኩር እንስሳት፤ የበኩር ምርት ለእግዚአብሔር የተለዩ ነበሩ፤ የተለዬ ዕጣንም ነበር። ከቀናተም በሳምንት፤ በዓመት፤ በሰባት ዓመት፤ በአምሳ ዓመት ለአምልኮ የተለዩ ቀናት ነበሩ። ህልየት (ሙዚቃም) የተለዬ ነበር :: ዝርዝር የዓምልኮ ሕግጋቱ የነበራቸው ዓላማ አንድና እርሱም እግዚአብሔርን ማክበር ነው።

አምልኮ በብሉይ ኪዳን አክብሮትንና ታማኝነትን ለእግዚአብሔር የምንገልጽበት ድርጊት ሲሆን የሚከናወነውም በተወሰነ ቦታና በታቀደለት ጊዜ ነበር። ለምሳሌ ያህል ኢየሩሳሌም የአይሁዳዊያን የአምልኮ ማዕከል ነበረች (ዮሐ 4:20.) ዳንኤልን ለአብነት ያህል ብንወስድ የእልፍኙ መስኮቶች ወደ ኢየሩሳሌም አንጻር ተከፍተው በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጕልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ይጸልይና ያመሰግን ነበር (ዳን:- 6:10):: በተጨማሪም በቤተመቅደስ፤ (መዝ 138:2) በመሰዊያው አካባቢ (1ኛ **ነገሥት** 18:22፣ ኢሳ 36:7)፤በበሩ አካባቢ (ኤር 7:2)

**ሐ. የምኩራብ አምልኮ**

ቤተ መቅደሱ ከተደመሰሰና አይሁዳዊያንም በመካከለኛው ምስራቅ ከተበታተኑ በኋላ አዲስ የአምልኮ ሥርዓት በምኩራብ ተጀመረ። የትኩረት አቅጣጫውም መስዋዕት ላይ ሳይሆን ቅዱሳት መጻህፍት ላይ ነበር። የምኩራብ አምልኮ በጸሎትን፤ምስጋናን፤መንፈሳዊ ትምህርትንም ሆነ ስብከትን ሲያካትት ማህበራዊ ኑሮም አንዱ ክፍል ነበር። ለአብነት ያህል የዓምልኮውን ይዘት በነህ:- 8:4-6 እንመልከት:-

"… ዕዝራም በሕዝቡ ሁሉ ላይ ከፍ ብሎ ሕዝቡ ሁሉ እያዩ መጽሐፉን ገለጠ፤ በገለጠውም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ቆሙ ፤ ዕዝራም ታላቁን አምላክ እግዚአብሔርን ባረከ፤ ሕዝቡም ሁሉ እጃቸውን እየዘረጉ። አሜን፥ አሜን ብለው መለሱ። ራሳቸውንም አዘነበሉ፥ በግምባራቸውም ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ…"

**መ. ሙዚቃ በቤተመቅደስ**

ዳዊት ከልጅነቱ ጀምሮ የሙዚቃ ልምድ እንደነበረው ከታሪኩ እናነባለን። የአባቱን በጎች በሚጠብቅበት ጊዜ ሙዚቃ እየደረሰ በክራር ዝማሬ አምላኩን ያመሰግን ነበር። የመዝሙሮቹ ስምም በግሪኩ ሳሎ ይባላል፤ ይህም ማለት በነጠላ አውታር ሙዚቃን መደርደር ማለት ነው። ንጉስ ከሆነም በኋላ ከፊሎቹን ሌዋውያን

በሙዚቃ መሳሪያ የአምልኮ መሪ አድርጓቸው እንደነበረ እናስተውላለን (1ዜና:- 23:5, 25:1-8):: ስለሆነም ሙዚቃ ከቋሚ የአምልኮ መሳሪያዎች አንዱ ሆኖ ተቆጠረ። ለአብነት ያህል መዝሙር 150ን ብንወስድ:-

"እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት፤ በኃይሉ ጠፈር አመስግኑት። በችሎቱ አመስግኑት፤ በታላቅነቱ ብዛት አመስግኑት። በመለከት ድምፅ አመስግኑት፤ በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት።

በከበሮና በዘፈን አመስግኑት፤ በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት። ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት፤ እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት። እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን። ሃሌ ሉያ።" ይላል።

**ሠ. ጌታ ኢየሱስና አምልኮ**

ጌታ ኢየሱስ ያደገው በገሊላ በመሆኑ ወደ ኢየሩሳሌም በስርዓተ ቅዳሴ ወቅት ቢሄድም የአምልኮ ጊዜውን ያዘወትር የነበረው ከቤተመቅደስ ውጭ በግልና በሕብረት ነበር። ስለ አምልኮ በአመርቂ ሁኔታ የገለጸበት ቦታ በዮሐ:- 4: 20-23 ያለው የሳምራዊቷ ሴት ታሪክ ነው።

ዕብራዊያን 22:28 እንደሚጠቁመን እግዚአብሔርን የምናመልከው ለርሱ ደስ በሚለው መንገድ እንጂ በራሳችን መንገድ አይደለም።

"ስለዚህ የማይናወጥን መንግሥት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃትእግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ" ደስ የሚሰኝበትን መንገድ የሚነግረን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። (...የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል...)

በመንፈስ መስገድ ማለት ከእርሱ ጋር ግንኙነት ማድረግ እንድንችል በተሰጠን መንፈሳችን ምላሽ መስጠት ነው። አምልኮ መንፈሳችን ለእግዚአብሔር መንፈስ መልስ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው። አምልኮ በእግዚአብሔር ደስ የመሰኘት ነገርም ስለሆነ ስሜቶቻችንም ይጨምራል። ማለትም እግዚአብሔር ስሜቶችን የሰጠን በማስመሰል ሳይሆን በጥልቀት እንድናመልከው ነው። በእውነት መስገድ (ማምለክ) ማለት እግዚአብሔር ለግላችን በሰጠን ልምድና ባሕሪ ለርሱ ያለንን ፍቅር በእውነት መግለጽ ማለት

**ረ. የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን**

በሐዋርያት ስራ:- 2:21-22 "ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤ በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቊረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።" ይህ ድርጊት ጌታ ላደረገላቸው አምልኳዊ ምላሽ ነው። በይበልጥ በቁጥር 26-27 እንደዚህ ተገልጿል:-

"በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።"

**ሸ. አምልኮ በጳውሎስ ዘመን**

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደገለጸው (ሮሜ 12:1) አምልኮ ሁለመናን ለጌታ መስጠት ነው። ባስተሳሰባችን፤ በስሜታችን፤ ለጌታ ክብር ስንኖር ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ተገዛን ማለት ነው፤ ይህም እውነተኛ አምልኮ ይባላል። አገልግሎታችን በቤተመቅደስና በጊዜ አይወሰንም። የትም ቦታና በመቼውም ጊዜ ልናገለግል እንችላለን። ምክንያቱም እኛው ራሳችን ቤተ መቅደስ ነንና።

ሐዋርያው በሮሜ 15:16ም "ነገር ግን አሕዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው የተወደደ መሥዋዕት ሊሆኑ፥ ለእግዚአብሔር ወንጌል እንደ ካህን እያገለገልሁ፥ ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ እሆን ዘንድ ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ ምክንያት ተመልሼ ላሳስባችሁ ብዬ በአንዳንድ ቦታ በድፍረት ጻፍሁላችሁ"፤ በማለት ማገልገል ራሱ አንዱ የአምልኮ ዓይነት እንደሆነ የገልጻል። በሮሜ:- 15:22 መሰረት ደግሞ ቁሳዊ ዕርዳታ ማድረግ ወይም የገንዘርብ ዕርዳታ መስጥት አንዱ እግዚአብሔርን ማምለኪያ መንገድ ነው።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. አቤልና ቃዔል በመስዋዕት እግዚአብሔርን ያመለኩት እንዴት ነበር ከዚህስ ምን እንማራለን ? (ዘፍ 4:1-6)
2. አብራሃም በሴኬም፤ በቤቴል፤ በሄብሮንና በሞሪያ ተራራ ላይ ያቀረበውን መስዋዕት ይዘርዝሩ ስለ አምልኮ ያስተዋሉትን ያካፍሉ:: (እንደ ምሳሌ በዘፍ 13:1-4; 22:1-19)

3. ባጠቃላይ ከሙሴ በፊት የነበሩ ሰዎች እግዚአብሔርን ያመለኩት እንዴት ነበር? በዘፍ 8 ና 9
4. በሙሴ ዘመን የነበረውን የአምልኮ ሂደት ተነጋገሩ::
5. የምኩራብ አምልኮ ስንል ምን ማለታችን ነው? ምንንስ ያጠቃልላል? በነህ:- 8:4-6
6. በሙዚቃ ስለ ማምለክ መዝሙር 150ን በመጠቀም ያብራሩ
7. ጌታ ኢየሱስ አብን ያመልክ የነበረው እንዴት ነበር
8. በሐዋርያት ስራ:- 2:26-27 መሰረት ሐዋርያት ጌታን ያመልኩት የነበረው እንዴት ነው?
9. በሮሜ:- 16ና22 መሰረት ጳውሎስ አምልኮን የገለጸው እንዴት ነበር?
10. በዛሬው ጥናት ያገኘነውን እናካፍል። ከዚህ በፊት ከምናውቀው የተለየ ነገር ምን አገኘን?

**ጥናት ሦስት**

**የአምልኮ መገለጫዎች**

**ዓላማ:-** መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአምልኮ መገለጫዎችን ለይተን ለመገንዘብና እውቀት በሌለው መልኩ ሳይሆን በመስጠትና

በመገዛት ማምለክ እንድንችል።

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዳሰሳ**

ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን ድረስ ብንዳስስ አምልኮ እግዚአብሔርን በመባረክ፤ እርሱንም በማወደስ፤ በፊቱ በመምበርከክና በመስገድ፤ በመዘርጋትም ሆነ ለጥ ብሎ እጅ በመንሳት ፤ ሃሴት በማድረግና በደስታ በመዝለል የሚገለጽ ለእግዚአብሔር ውለታ ምላሽ የመስጠትና የመገዛት ተግባር ነው። ይህም ይህም ከብዙ በጥቂቱበሚከተለው ሁኔታ ይገለጻል።

**ሀ) በብሉይ ኪዳን**

**መባረክ -** መዝ:- 34:1 ፤ 1ኛ ዜና:- 29:20
እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፥ ምስጋናውንም ዘወትር በአፌ ነው።

‘‘ዳዊትም ጉባኤውን ሁሉ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ባርኩ አላቸው። ጉባኤውም ሁሉ የአባታቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ባረኩ፥ ራሳቸውንም አዘንብለው ለእግዚአብሔርና ለንጉሡ ሰገዱ።’’

**ማወደስ -** መዝ 22:23; 61:8
እግዚአብሔርን የምትፈሩ፥ አመስግኑት፤ የያዕቆብ ዘር ሁላችሁ፥ አክብሩት፥ የእስራኤልም ዘር ሁላችሁ፥ ፍሩት።

**መንበርከክ -** መዝ:- 29:2
የስሙን ክብር ለእግዚአብሔር አምጡ፥ በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ።

**መዘመር** - መዝ:- 66:2
ለስሙም ዘምሩ፥ ለምስጋናውም ክብርን ስጡ።

**መስገድ/ ለጥ ብሎ እጅ መንሳት -** ዘፍ:- 24:26፤ ዘጸ:- 4:31፤ ኢያ:- 5:13-15
(… ኢያሱም ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና። ጌታዬ ለባሪያው የሚነግረው ምንድር ነው? አለው። የእግዚአብሔርም ሠራዊት አለቃ ኢያሱን። አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ አለው። ኢያሱም እንዲሁ አደረገ።) ኢያሱ 5:13-15

**ለ) በአዲስ ኪዳን**

1. **ስብከትና ትምህርት -** 2ኛ ጢሞ:- 4:2

ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለ ጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገሥጽ ምከርም።

**2. የጌታራት -** 1ኛ ቆር:- 11:23-26፤ ማቴ:- 28:19

"ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቈርሶም። እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ። ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።

**3. ጸሎት -** ዮሐ:- 18 ፤ 1ኛ ጢሞ:- 2:1 - 2

እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።

**4. ቃሉን ማንበብና ማጥናት -** 1ኛ ጢሞ:- 4:13

እስክ መጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ።

**5. ዝማሬናሙዚቃ -** ቆላ 3:16 ፤ ዕብ:- 13:15 ፤ 1ኛ ተሰ:- 5:16-18

የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።

**6. እርዳታመስጠት -** ዕብ:- 13:16 ፤ ፊል:- 4:18 ፤ ያዕ:- 1:27

ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።

ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፥ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው።

የአዲስ ኪዳን አምልኮ መገለጫዎችን ሰብሰብ አድርገን እንደሚከተለው ማስቀመጥ እንችላለን፤፡

- **ለእግዚአብሔር መናገር**

የአንድ አካል ብልት በመሆናችን እግዚአብሔርን በዜማ መሳሪያና በዝማሬ እያደነቅን እናመሰግናለን፤በሕብረት ጸሎት ተግተን እናደንቀዋለን እንለምነዉማለን፤ ለሚያስፈልጋቸዉም በመለገስ (ወላጆች የሌላቸውን ልጆችና ባልቴቶችን:- ያዕ 1:27) ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ እናቀርባለን።

- **እግዚአብሔርን መስማት**

እግዚአብሔር በልዩ ልዩ መልኩ ሲናገረን መስማትና በተግባር መተርጎም አስፈላጊ ነው። እርሱ ሲያነሳሳንና ማንነቱን በየዕለቱ ሲገልጽልን ትክክለኛውን አምልኮ ለማቅረብ ኃይል ይሆንልናል። የኃይሉን ታላቅነት በይበልጥ ስንረዳ፤ፍቅሩንና ባህሪውን ስናስተውል ክብር የሚገባው መሆኑን ተገንዝበን በመንፈስና በእውነት ማምለክ እንጀምራለን። (ኢሳ:- 6:1-8)

- **ምላሽ መስጠት**

ስለ እግዚአብሔር ማንነት፤ ስላደረገልንና ስለሚያደርግልን ነገር፤ባወቅንና በተገነዘብን ቁጥር በተግባር ምላሽ ስንሰጥ የሚገባውን እግዚአብሔርን ማምለካችን ነው። (ኢሳ:- 6:1-8)

እንግዲህ ልባችን በቃልና በዜማ ራሱን ሲገልጽ፤አዕምሮአችን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ለመለዬትና እንደፈቃዱ ለማደረግ ሲመረምር፤አካላችንም ለተግባራዊ ክንውኑ ራሱን አዘጋጅቶ ሲገኝ እግዚአብሔርን እያመለክን ነው።

- **እውነተኛ ስሜት**

አምልኮ በእግዚአብሔር ደስ የመሰኘት ነገርም ስለሆነ ስሜቶቻችንም ይጨምራል። ሆኖም እግዚአብሔር ግብዝነትን ስለሚጠላ በጥልቅ ስሜት ልናመልከው ይገባል እንጂ በማስመሰልስሜትመሆን የለበትም። ስለዚህ አምልኮ ትክክልም እውነተኛም መሆን አለበት።

እውነተኛ ስሜት ደስታን እንደሚያስከትል የሐዋርያት ሥራ 2: 42, 46 እንደዚህ ይገልጸዋል:- ‘‘በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር። በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር’’

***የመወያያ ጥያቄዎች***

አምልኮእንዴትይገለጻል

1. በብሉይ ኪዳን ለአብነት የተዘረዘሩ ምሳሌዎቸን ያብራሩ::
2. እግዚአብሔርን የምንባርከው እንዴት ነው? (ዘዳግም 8:10; መዝ. 34:1; 96:2-3; 103: 1- 6)
3. ለእግዚአብሔር ለጥ ብሎ እጅ መንሳት ምንን ያመለክታል ? (ዘፍ:- 24:26፤ዘጸ:- 4:31፤ኢያ:- 5:13-15)
4. በጥናቱ መሰረት በአዲስ ኪዳን የአምልኮ መገለጫዎችን ያብራሩ::
    - 2ኛ ጢሞ:- 4:2
    - ቆላ 3:16 ፤ ዕብ:- 13:15 ፤ 1ኛ ተሰ:- 5:16-18
    - 1ኛ ቆር:- 11:23-26፤ ማቴ:- 28:19
    - 1ኛ ጢሞ:- 4:13
    - ዮሐ:- 18 ፤ 1ኛ ጢሞ:- 2:1 - 2
    - ዕብ:- 13:16 ፤ ፊል:- 4:18 ፤ ያዕ:- 1:27
5. በያዕ:- 1:27 መሰረት ንጹህ የሆነና ነውር የሌለበት አምልኮ ምን ዓይነት ነው?
6. ክርስቲያን ቃሉን ሲያነብና ሲያጠና እግዚአብሔርን የሚያመልከው እንዴት ነው?
7. በአምልኮ ሂደት ውስጥ ለእግዚአብሔር መናገር፤ እግዚአብሔርን መስማት፤ ምላሽ መስጠትና እውነተኛ ስሜት የተባሉትን አባባሎች ያብራሩ::
8. ከጥናቱ የቀረልዎትን ያካፍሉ::

***መደምደሚያ***

የአዲስ ኪዳን አምልኮ መገለጫዎችን ሰብሰብ አድርገን ለእግዚአብሔር መናገር፤ እግዚአብሔርን መስማት፤ ምላሽ መስጠትና እውነተኛ ስሜትን በመግለጽ ላይ ያተኮሩ ናቸው ማለት እንችላለን:: እግዚአብሔርን መለመን፤በልዩ ልዩ መልኩ ሲናገረን መስማትና በተግባር መተርጎም ፤ ስለ እግዚአብሔር ማንነት፤ ስላደረገልንና ስለሚያደርግልን ነገር፤ ባወቅንና በተገነዘብን ቁጥር በተግባር ምላሽ መስጠትና በመንፈሳዊ ስሜት በፊቱ መደሰት የዘወትር ተግባራችን ሊሆን ይገባል::

## ጥናት አራት

## እውነተኛ አምልኮ

**ዓላማ:-**

እግዚአብሔር እውነተኛ አምልኪዎችን ስለሚፈልግ እርሱን በማወቅ ከልማዳዊ አምልኮ ባለፈ መልኩ በመንፈስና በእውነት ማምለክን እንድን ለማመድ::

**መግቢያ:-**

ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ የሚቻለው በክርስቶስ ኢየሱስ አማካኝነት ብቻ ሲሆን ከልብ የሆነ አምልኳችንም የሚከናወነው በመንፈስ ቅዱስ አስቻይነት ብቻ ነው።ይህንን ስንል መንፈስቅዱስ፥ "አባ አባት ብለን የምንጮህበትን የልጅነት መንፈስ" በልባችን ይልካል (ገላ 4:6):: ያም መንፈስ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይመሰክራል (ሮሜ 8):: ይህ የመንፈስ አንድነትም ነው እግዚአብሔርን እንደ ፈቃዱ እንድናመልከው የሚያስችለን።

በማይሰማ መቃተትም ይጸልይልናል (ሮሜ 8:26) ይህም ማለት ጌታ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሆኖ ጌታ ኢየሱስን ከፍ ከፍ እንድናደርገውና እንድናመልከው ያደርገናል። ስለዚህ የአምልኮ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ላይና ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ከዚህ ውጭ የሆነ እንቅስቃሴ የአመላለክ ሁኔታ ላይ ያተኮረና ሕይወት የለሽ ስርዓት ብቻ ነው።

**ልዩ ልዩ አምልኮ**

ጌታ ኢየሱስ ለሳምራዊቷ ሴት ስለ ሦስት ዓይነት አምልኮ ሲያብራራ እንመለከታለን። ይኸውም:-

1. “እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ ዮሐ 4:22) በማለት ያለ ዕውቀት ስለሆነው የሳምራውያን አምልኮ፤
2. “እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን ፤፡ ዮሐ:- 4:22) በማለት በዕውቀት ስለሆነውና አዳኙን ስላላስተዋለው የአይሁዳውያን አምልኮ፤
3. “ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና ፤፡ ዮሐ :- 4:23) በማለት ስለ እውነተኛ አምልኮ::

ሳምራውያን አምስቱን የሙሴን መጽሐፍ በመጠቀም ስለ እግዚአብሔር ጥቂት ዕውቀት እንደነበራቸው የስነ መለኮት ሰዎች ይናገራሉ። በአንጻሩ አይሁዳዊያን ደግሞ በብሉይ ኪዳን መሰረት ብቁ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት እንደነበራቸው

ግልጽ ነው። ሆኖም ግን በእውነትና በመንፈስ አልነበረም። በዚህ ዘመንም ያለው የአምልኮ አይነት ከዚህ አመዳደብ ጋር የሚመሳሰል ነው።

‘‘ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል’’ ዮሐ:- 4: 23-24

**ስፍራ የማይገታው አምልኮ**

ለሳምራዊቷ ሴት ጌታ ኢየሱስ ስፍራ የማይገታው አምልኮ ጊዜ እንደ መጣና ወቅቱም በዚያኑ ዕለት እንደነበረ ገለጸላት። ጌታ ኢየሱስ ይህንን ማለቱ አምላካችንን በቦታ፤ በአካባቢና በውጫዊ ነገሮች ሳንለካና ሳንገድብ በጊዜውም አለጊዜውም ውስጣችን በፈሰሰው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ማምለክ እንደምንችል ማሳየቱ ነው (ዮሐ:- 4:21)

**በመንፈስ ማምለክ**

በመንፈስና በእውነት ስንል ግን ምን ማለት ነው ? መልሱን ዮሐ:- 4:24 ላይ እናገኛለን። ‘‘እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል’’

ከዚህ ጥቅስ የምንገነዘበው ተመላኪውና አምላኪዎቹ ስምምነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ነው። ‘‘እግዚአብሔር መንፈስ ነው’’ ስንል በቦታና በጊዜ የማይወሰን ወሰንና ዘመን የለሽ ነው ማለታችን ነው።

አምላኪዎቹም ከእርሱ ጋር እስከተስማሙ ድረስ መንፈሳዊነት እንጂ የቦታና የጊዜ ገደብ ሊወስናቸው እንደማይችል ልንገነዘብ ያስፈልጋል።

ሌላው ሃሳብ በመንፈስ ማምለክ ማለት የአምልኮው ምንጭ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ነው ፤ መንፈስንም የሚሰጥ እርሱ ነው። ለዚህም ነበር መንፈስ ቅዱስን በመስጠት ለመንፈሳዊ አምልኮ ብቁ ያደርገን ዘንድ ጌታ ኢየሱስ የተላከው።

ጌታ ኢየሱስ ትክክለኛ አምልኮ ከራሱ እንደሚመነጭ ሲገልጽም:- ‘‘ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል’’ ዮሐ:- 4:23 በማለት የተናገረው።

ጌታ ኢየሱስ ከዋጀንና የልጅነትን መብት ካገኘን በኋላ ነበር እግዚአብሔር አብ አባ አባ ብለን የምንጮህበትን መንፈስ የሰጠን። ስለዚህም በመንፈስ ማምለክ ማለት አብን በክርስቶስ መንፈስ የምናመልክበት የልጅነት መንፈስ ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክን እንደ አባት ማምለክ የልጅነት መንፈስ ለተሰጣቸው ብቻ ነው። ደግሞም በመንፈስ ማምለክ ማለት ወልድ አብን ለገለጸላቸው ነው።

**በእውነት ማምለክ**

በእውነት ማምለክ የሚለው አባባል በቅንነትና በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ከሚለው የላቀ መለኮታዊ ተረጉም አለው። መጽሐፉ ሕግ በሙሴ እንደተሰጠና ፀጋና እውነት ግን በክርስቶስ እንደሆነ ይነግረናን። ጌታ ኢየሱስ ፥እኔ እውነትና ሕይወት ነኝ አለ። በብሉይ ኪዳን ሁሉ ነገር ጥላና ተስፋ ነበር፤ በክርስቶስ ግን እርግጠኛና ጭብጥ ነው። ኢየሱስ ፀጋና እውነትን የተሞላ ነው። መንፈስ ቅዱስም የእውነት መንፈስ ነው።

አምልኮ የእግዚአብሔር ጌታነት፤ ኃያልነት፤ ክብሩና ዉበቱ ሲታየን የምናቀርበው የፍቅርና የአክብሮት ልባዊና ውጫዊ ስግደት ነው። ስለሆነም እውነተኛ አምልኮ ማለት ለእግዚአብሔር የሚገባውን ምስጋናና ውዳሴ፤ መፈራትና ክበር፤ ቅድስናና ንጽህና በታላቅ አክብሮት በእውነትና በመንፈስ ማቅረብ ማለት ነው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ሰው ማምለክ ያለበት ለምንድን ነው? (ዮሐ:- 4:23)
2. የትክክለኛ አምልኮ ማዕከሉ ማን ነው? (ዮሐ:- 4:22) ስለዚህ ምን እናድርግ?
3. እውነተኛ አምልኮ ምን ዓይነት ነው? እንዴትስ ይገለጣል? ((ዮሐ:- 4:23-24)
4. በዮሐንስ 4:23-24 መሰረት የዕውነተኛ አምልኮ ሶስቱ ባህሪያት እነማን ናቸው?
5. አምልኮን/ስግደትን ከመቀበል አኳያ በማቴ:- 14:33 እና በሐዋ:- 10:25-26 ምን ልዩነት አለ?
6. በጥቅሶቹ መሰረት እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች ምን ምንን ሊያመልኩ ይችላሉ፣ (ቆላ 2:18፣ የሐዋ:- 7:43, 10:25-26, ሮሜ 1:25፣ ማቴ 4:9)
7. በእውነት መስገድ ማለት ምን ማለት ነው? በዘዳግ:- 6:4-5 መሰረት እውነተኛ አምልኮ እንዴት ይገለጻል?
8. ጌታ ኢየሱስ ስፍራ ስለማይገታው አምልኮ/አገልግሎት ለሳምራዊቷ ሴት እንዴት ገለጸላት?
9. በዚህ ጥናት መሰረት ልዩ ልዩ አምልኮን ተወያዩ። የጥናቱስ ዓላማ ምንድ ነው።
10. በማር 12፥30 “አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት”። ይህ ጥቅስ ስለ አምልኮ ምን ያስተምረናል?

***መደምደሚያ***

እውነተኛ አምልኮ እግዚአብሔር ደስ በሚለው መልኩ እናመልከው ዘንድ በመንፈሱ የሚገልጽልንና የምንተገብረው መንፈአዊ እውነት ነው።

## ጥናት አምስት

## ተያይዞ ማምለክ

**ዓላማ፡-** እግዚአብሔርን ተያይዞ የማምለክን ጠቀሜታ ማሳሰብ::

**መግቢያ፡-**

እግዚአብሔር በፍጥረቱ ይገለጻል። ፈጥረት ሁሉ ውበቱንና ግርማዊነቱን ያሳያል። ሰዎችንም ሲፈጥረን በእርሱ ደስ እንዲለንና አስገራሚነቱን እንድናደንቅ ነው። እርሱ ፈጠረን፤ አዳነን፤ እየተንከባከበንም ነው። ተያይዘን ማምለክ ያለብንም ለዚህ ነው።

- **መጽሐፍ ቅዱሳዊ አምልኮ**

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አምልኮ ለተመላኪው ለእግዚአብሔር ከአምላኪው ከሰው ልጅ የሚሰጥ አክብሮት፥ ልዕልና ዕውቅና ሙገሳና፥ ቡራኬ ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ በተለያዬ መልኩ ተገልጾ ይገኛል። እግዚአብሔር በፍጡራኑ ሁሉ የሚመለክ ቢሆንም (ራዕ፡ 5: 9-14) በአምሳሉ ከተፈጠረና በኃጢአት ምክንያትም ሊደርስበት ከነበረው ዘላለማዊ ሞት አምልጦ ከዳነ ሰው ግን ይበልጥ ይፈለጋል። እንግዲህ ክርስቲያኖች ተያይዘን ስናመልክ እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል፤ ሁሉን የሚያውቅ፤ በሁሉ ቦታ የሚገኝ፤ የማይለወጥ፤ ችሎታው የማይመረመር፤ መንገዱ የማይታወቅ፤ ሃሳቡም ከሰው ሃሳብ የተለዬ መሆኑን በመንፈሳችን ተገንዝበንና ክብርን እየሰጠን መሆን ይኖርበታል። በእውነተኛው የልብ ደስታና ሃሴት ልናከብረው ያስፈልጋል።

- **ብቸኛው ተመላኪ**

መዝ፡-100: 1-5 እንዴት ማምለክ እንዳለብን ጥሩ ምሳሌ ነው::

‘‘ምድር ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር እልል በሉ ፥ በደስታም ለእግዚአብሔር ተገዙ፥ በሐሤትም ወደ ፊቱ ግቡ ። እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ እወቁ፤ እርሱ ሠራን እኛም አይደለንም፤ እኛስ ሕዝቡ የማሰማርያውም በጎች ነን ። ወደ ደጆቹ በመገዛት፥ ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ፤ አመስግኑት፥ ስሙንም ባርኩ ፤ እግዚአብሔር ቸር፥ ምሕረቱም ለዘላለም፥ እውነቱም ለልጅ ልጅ ነውና።’’ እግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣን፤ በሰራው ፍጥረት ሁሉ ላይም ሥልጣንን የሰጠን በመሆኑ ብቻውን ሊመለክ እንደሚገባው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ከዐስርቱ ትዕዛዛት የምጀመሪያው የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ነው። እንዲህ ይነበባል፡-

‘‘ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ’’ (ዘፀ አት፡- 20:3)፡፡ እግዚአብሔር አምላክን አውቀነውና በመረዳት የምናመልከው እንጂ በልዩ ልዩ ምስል ወክለን (ዘዳ፡ 4:15-24) ወይም እንደማይታወቅ አምላክ ቆጥረን (የሐዋ 17: 23-26) የምንነዛለት አይደለም። በዘዳ:- 4:35 እንደዚህ ይላል:- ‘‘እግዚአብሔርም አምላክ እንደ ሆነ ታውቅ ዘንድ ይህ ለአንተ ተገለጠ፤ ከእርሱም ሌላ አምላክ የለም።’’

- **አምልኮ እንደ ትዕዛዝ**

በሌላ መልኩ ትዕዛዝ በመሆኑ ሌላውንና የማይገባውን አምላክ ማምለክ አይኖርብንም። ‘‘ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ’’ ተብሎ ተጽፏልና። ሌላ አምላክ ወይም ሌሎች አማልክት ሰውን አልፈጠሩም አላዳኑምም ስለዚህ ለጌታ የሚገባውን አምልኮ ሊያገኙ ወይም ሊሰገድላቸው አይገባም። በአንጻሩ ጌታችንን በመያያዝ እንድናመልክ ታዘናል። ኤፌ:- 5:19-20 እንደዚህ ይላል:- ‘‘በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤ ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።’’

- **ለእኩል ቤዝዎት የሕብረት እምልኮ**

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለውና እውነትም እንደሆነው በውድ ልጁ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን ማለትም የበደላችን ስርየት ያገኘን በመሆኑ አምላካችንን በሕብረት ልናመልክ ይገባናል።

በራዕይ ምዕራፍ 4ና 5 የተገለጸው አምልኮም ግዙፍ የሕብረት አምልኮ እንደሆነ እንገነዘባለን። ይህ አምልኮ በጌታ ፍጹማን የሆኑ ቅዱሳን በስሙሙ ሕብረት አምላካቸውን ከፍከፍ የሚያደርጉበት ትዕይንት ነው። የኛም የመያያዝ ዓላማ ይህን ክብርና ውዳሴ የተገባው አምላክ ለማምለክና ከፍ ከፍ ለማድረግ በመሆኑ እጅግ አስፈላጊ ነው።

- **በመልካም ሥራ ለመያያዝ**

‘‘ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር። በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።’’ የሐ:- 2:44-47

ለበለጠ ውጤትና መስፋት፤ ቃሉን በግልጽ ለማወጅ፤ ለተለዩ አገልግሎትና የሚደረስ ቦታ እንደጌታ ፈቃድ ለመለየት ተያይዞ ማምለክ አስፈላጊ ነው። (የሐ:- 4:24-35, 12:1-18, 13:1-3)

‘‘እነርሱም በሰሙ ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ ... ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ ... (የሐ:- 4:31)

መያያዝ ለመልካም ነገር ይቅርና ለመጥፎ ነገርም እንኳ ውጤትን የሚያስገኝ ስለመሆኑ በዘፍ 11ና የሐ5:1-11 ያለውን ታሪክ ብንመለከት ይበቃል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በራዕ 5:9-14 መሰረት በሰማይ ቤት ጻድቃንና መላዕክቱ እግዚአብሔርን የሚያመልኩት እንዴት ነው?
2. በዮሐ:-4:23-24 እና በሌሎችም ጥቅሶች መሠረት እግዚአብሔርን አውቀነውና በመረዳት ማምለክ ይኖርብናል ስንል ምን ማለታችን ነው? ተወያዩ
3. 1ዮሐ:-1:3 መዝ 133:1-3 በማንበብ አማኞች ከሌላው ፍጡር ይልቅ የህብረት አምልኮ ለምን አስፈለጋቸው?
4. በደስታም ለእግዚአብሔር መገዛት፤ በሐሤትም ወደፊቱ የመግባት ምክንያቱ ምንድን ነው? (መዝ:-100: 1-5)
5. በዘዳ፡ 4:15-24ና በየሐዋ 17: 23-26 መሰረት የእነዚህ የሕብረት አምላኪዎች ችግር ምን ነበር?

6. በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ከአባቶች እንደምንረዳው (የሐ:-4:31) ተያይዞ በጸሎት ማምለክ ምን ውጤት ያስገኛል?
7. በማቴ:- 12:25ና በማር:- 3:24 መሰረት መከፋፈል (አንድ ልብ አለመሆን) ምን ውጤት እንደሚኖረው ተወያዩ::
8. በአፍራሽ መልኩ እንኳን ውጤት ሊያመጣእንደሚችል በዘፍ:- 11:6ና በሐዋ:- 5:9 መሰረት ተወያዩ::
9. እንደ ሐዋርያቱ ዘመን ሁሉንም በጋራ አድርጎ ጌታን በጋራ ማምለክ አሁን የማይቻለው ለምን እንደሆነ ተወያዩ::
10. ከዛሬው ጥናት ምን ቀረልዎት?

***መደምደሚያ***

በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራን በእግዚአብሔርም እውቀት እያደግን (ቆላ:-1:10-11) በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሃይማኖት አብረን እንድንጋደልና በአንዱም መንፈስ እንድንቆም (ፊል:-1:27)ተያይዞ ማምለክ ወሳኝ ነው::

## ክፍል ሦስት
## ማደግ
## ጥናት 1
## መንፈሳዊ ዕድገት

ከ2014 -2016 በቤተ ክርስቲያናችን የአገልግሎት መርኃ ግብር ከታቀደው እንያያዝ:- ለማምለክ ለማደግ እና ለመሄድ ከሚሉት ቃላት ‘‘ማደግ’’ የሚለውን ቃል በዚህ ጥናት እናጠናለን።

**የንባብ ክፍል ዮሐ 15፡1-27**

***የጥናቱ ዓላማ***

በሥጋ እንደምናድግ በመንፈሳዊ ስብዕናችንም እንድናድግ የጌታ ቃል ስለሚያዘንና በዚህም ምድር በመንፈስ ስኬታማ ህይወት በመኖር እምነታችን ያደገና የጸና መሆን እንዳለበት ለማሳየት

***መግቢያ***

**አንድ ህጻን ልጅ የተለያዩ ችግሮች ከሌሉት በስተቀር ሲወለድ ማደግ ይጠበቅበታል። ህጻኑ ይበላል፣ይጠጣል፣የሰዎችን እርዳታ ያገኛል፤ ነገር ግን የእድገት ለውጥ ባይኖር ብዙዎቻችንን ደስተኞች አያደርገንም። ከተወለደ ጀምሮ በየዓመቱ አንድ ዓይነት ብስለት ውስጥ ቢኖር ምን ስሜት ይሰማናል?** የአማኝ ህይወት ለዕድገት የተጠራ ህይወት ነው። የማቴ ወንጌል 28፡19 ከሚያዛቸው ነገሮች አንዱ አማኞችን ደቀ መዝሙር በማድረግ ለመንፈሳዊ ህይወት እድገት ማብቃት ነው።ደቀ መዝሙር ማድረግ ነው ብለን ስንል እኛም ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ነው። ይህጥናትበዮሐ 15 ላይያተኮረሲሆን በተጨማሪ ገላ 5:22 እና ኢሳ 5፡1-10 እንድናጠና ይጥይቀናል።

ዮሐ 15 ለማደግ በግንዱ መኖር፣ ከአማኞች ጋር በፍቅር መኖርንና እንደ አማኝ በዓለምም ስለ ክርስቶስ ምን እንደሚገጥመንና እንዴት ማሸነፍ እንደምንችል በአትኩሮት ያስተምረናል።በጥቅሉ በዚህ ጥናት እንደ ጌታ ተከታዮች በመንፈሳዊ ህይወት ለማደግ ምን እናድርግ የሚሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል።

***መንፈሳዊ ዕድገት እና መንፈሳዊ ፍሬ***

የዮሐንስ ወንጌል 15፡1-27 በሶስት የተከፈለ ሲሆን ማለትም **ከቁ.1-11፤12-17 እና 18-27** ናቸው። በዚህ ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርት ጋር ህብረት ወይም ኮንፈረንስ ያደረገበት ጊዜ ነበር። **እንዴት ማደግ ይቻላል?**

i. ከክርስቶስ ባለመለየት እና አብሮ በመኖር **(ዮሐ 15፡1-11)**

ዮሐ 15፡1-6 ቅርንጫፍ ፍሬ ለማፍራት ከግንዱ ጋር መጣበቅ ወይም መኖር እንዳለበትአማኝም በመንፈሳዊ ህይወት ለማደግ ከግንዱ ከክርስቶስ ጋር መያያዝ/መኖርእንዳለበት ያስተምራል። ቃሉ በግልጽ እንዳስቀመጠው **<u>በገበሬ</u>** የተመሰለው አብ ሲሆን <u>በግንዱ</u> የተመሰለው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። በተጨማሪም ቅርንጫፎቹ ደግሞ እኛ ነን።

በዚህ በመጀመሪያ ክፍል **<u>መኖር (remain)</u>** የሚል ቃል ብዙ ተደጋግሞ ይገኛል። በዚህ ወቅት ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በህይወታቸው እንዲያድጉ ወይም ፍሬ እንዲያፈሩ ኮንፍረንስ በማድረግ ይህን ትምህርት በትኩረት አስተማረ። ‘‘ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል’’ (15፡2)፦ በዚህ ጥቅስ ‘‘ፍሬ ማፍራት’’የሚለውን ትምህርት በቀጥታ ከገላ 5፡22 ጋር አገናኝቶ ማጥናት የተሻለ እውቀት ይሰጠናል። ‘‘የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው’’ (በዚህ ጥናት በተለያዩ ቦታዎች ስለ እነዚህ መንፈሳዊ ፍሬዎች እናነሳለን)።በእርሱ እንድንኖር የሚጠይቀን ዋናው አስተማሪያችን እራሱ ክርስቶስ ነው። ከእርሱ ተለይቶ ለመኖር መሞከር ላለማደግ ዋናው ምክንያት ነው። ገበሬው ያለፍሬ ያለውን ዛፍ በሂደት መቁረጡ አይቀርም።

**ቁ.7-11 መሰረት በጌታ ወይም በግንዱ መኖር ማለት**

- **በቃሉ መኖር** ነው፦ አማኝ ከዳነ በኋላ ሌላው ትምህርት በቃሉ የመኖር ትምህርት ነው። እግዚአብሔር አባታችን በልጁ ሞትና ትንሳዔ በከፈተልን በር የእርሱን ቃል እንድንሰማ፣እንድናነብ እና ሌሎችም እንዲያስተምሩን ሆኗል። ይህም የሆነው በታላቅ ጸጋው ነው። ነገር ግን ባነበብነውና በሰማነው ቃል በየቀኑ መመላለስ **<u>ዋናው በመንፈስዊ ህይወት የማደግ ምልክት</u>** ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች እንደሚከተለው ይላል ‘‘መጥቼ ባያችሁ ወይም ብርቅ፥ በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሃይማኖት አብራችሁ እየተጋደላችሁ፥ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ ስለ ኑሮአችሁ እሰማ ዘንድ፥ <u>ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ</u>’’ (ፊል 1፥27)። በወንጌል መኖር ማደግ ነው። ቁ. 11 እንደሚነግረን ልጁ ለአባቱ እንደታዘዘ አማኞችም መታዘዝ አለብን። በዚህ ጊዜ ፍጹም ደስታና እድገት እናገኛለን።
- **እንደቃሉ የሆነ ልመና መለመንና ማግኘት** (በክፍሉ መሰረት)፦የሚያድግ አማኝ ጸሎት ሲጸልይ ጸሎቱ እንደ ጌታ ቃል መሆኑን ይመረምራል። ጊዜውን አያባክንም፤ወደ እሳት ከመጣልም ይጠበቃል።
- **አብን የሚያስከብር ነገር ማድረግ** ነው፦ በመሆኑም የህይወት እድገት ወይም ፍሬ ማፍራት አብ እንዲከበር ያደርጋል።ይህም በውስጣችን ደስታን ይፈጥራል።

**2. ከሌሎች አማኞች ጋር በእውነተኛ ፍቅር በመኖር**(ዮሐ 15፡12-17በተጨማሪ 1ኛ የዮሐንስ መልእክት በግላችሁ አጥኑ )

ከሌሎች ጋር ያለን ክርስቲያናው ፍቅር የማደግ ምልክት ነው። አንድ ፍሬ የሚያፈራ አማኝ እያደገ መሆኑን ወይም በጌታ መኖሩን የሚያረጋግጠው ለአማኞች ባለው መውደድ ነው። አጠገባችን ያሉትን ወገኖችን ሳንወዳቸው አማኝ መሆናችንን ማረጋገጥ አስቸጋሪ ትምህርት ነው። የዚህ ክፍል ቁልፍ ቃል ‘‘መዋደድ ነው’’። በዮሓ 15፡12-13 መሠረት ጌታ እውነተኛውም ፍቅሩን ያሳየን **<u>ነፍሱን በመስጠት</u>** ስለሆነ የአማኝ ፍቅር መስዋዕትነት የሚጠይቅ ይሆናል። ክርስቶስ ወዳጃችን እንዲሆን ከፈለገ አማኝ ሌሎችን መውደድ አለበት። ‘‘ ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል’’ (ሮሜ 5፡8)። ብዙ አገልግሎት ቢኖረንም እውነተኛ ፍቅር ከሌለን ዋጋ እንደሌለው 1ቆሮ 13 በጥብቅ ያስተምረናል።

**3. በዓለም እንዴት እንደምንኖር በማወቅ (ዮሐ 15፡18-27)**

በማደግ ላይ ያለ አማኝ በዓለም ስላለ በዓለም እንዴት እንደሚኖር ማወቅ አለበት። ስለ ጌታ መጠላት ሲደርስበት ይህ ሊሆን እንደሚችል ማወቅ አለበት። ስደት ሲደርስበት አማኝ መደንገጥ የለበትም። የጥላቻውም ምክንያት 1ኛ. በዓለም ስላሉ ከመንፈሳዊ ዓለም ነገሮች የአመለካከትና የእውቀት ለውጥ መኖሩ 2ኛ. የክርስቶስ ተከታይ መሆናቸው (ሰዎች ከሰይጣን ግዛት ስለሚላቀቁ ግጭት ይነሳል) 3ኛ. ኃጢአትን ስለሚገልጡ (መጥምቁ ዮሐንስ በዚህ ምክንያት ተሰውቷል)። በጎች በፍየሎች መካከል ይታወቃሉ።ነገር ግን እውነተኛውን የሚመሰክር መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር እንዳለ እርግጠኞች ነን።እርሱም ይረዳናል (ዮሐ 16፡1-2፣ 24-26)። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ለዚህ ጥሩ ትምህርት ይሰጣል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. መንፈሳዊ ህይወት ዕድገት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የአማኝ የህይወቱ እድገት ከዮሐ 15 ጋር እንዴት ይገናኛል?
3. በዮሐ 15፡1-5 የተጠቀሱ ምሳሌያዊ ነገሮችን አብራሩ (ገበሬ፣ግንዱ፣ቅርንጫፍ፣ፍሬ ማንና ምንድ ናቸው?)
4. ዮሐ 15፡1-11 ዋና ፍሬ ሀሳብ ምንድ ነው? ተወያዩ
5. ዮሐ 15፡12-17 መሰረት አማኝ ለማደግ ምን ማድረግ አለበት (ሌላ ተጨማሪ ማብራሪያ ከገላ 5፡22 ቢጠቀስ ጥሩ ይሆናል)
6. ዮሐ 15፡19-27 መከራና የክርስቲያን እድገት እንዴት ይገናኛል? እንዴትስ እንወጣለን?
7. የዚህ ጥናት ዋናው ዓላማ ምንድ ነው?
8. በዮሐ 15 መሰረት ህይወታችንን ስናይ ምን መሻሻል አለበት ትላላችሁ?

**መደምደሚያ**

በጌታ የዳነ አማኝ የሂደት ህይወት እንደሚኖር የማይካድ እውነት ነው።አንድ ዛፍ በሂደት ጊዜ ያድጋል፣እናም ያፈራል።የሰው ልጅ ይወለዳል፣ያድጋል፣ያፈራል። ነገር ግን ዛፍ ካላደገና ካላፈራ ይቆረጣል፣እድሉም መጥፋት ይሆናል። የሰው ልጅም ተውልዶ ባያድግ አያስደስትም። ላለማደግ ምክንያት በእርግጥ አንድ ችግር ሊኖር እንደሚችል የተረጋገጠ ነው።ስለዚህ ለአማኝ ከጌታ ጋር በቃሉና በጸሎት፣ከአማኞች ጋር እውነተኛ የፍቅር ኑሮ በመኖር እና በዓለም ስለክርስቶስ መከራ በመቀበል በጽናት መኖር መንፈሳዊ እድገት ነው።

## ማደግ
## ጥናት 2
## የአማኝ እድገት በዕብራውያን መልዕክት

### የንባብ ክፍል (ዕብ 5፡11-14)

የአማኝ እድገት **ለምን አስፈለገ?**

**ዓላማ**

በጌታ ቤት በቆየን መጠን ብስለት ያለን አማኞች እንድንሆን ጌታ  እንደሚፈልገን ለማሳሰ ብና መንገዱን ለማሳየት

**መግቢያ**

የዕብራውያን መልዕክት ቁልፍ ቃል ይበልጣል፣ይልቃል፣ ወይም ይሻላል ነው። እነዚህ ተመሳሳይ ቃላቶች ናቸው። ምን ወይም ማን ይሻላል ለሚለው ጥያቄ መልሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከምን ወይም ከማን ለሚለው ጥያቄ ደግሞ መልሱ በብሉይ ኪዳን ከተጠቀሱ መላእክት፣አገልጋዮችና አገልግሎት ነው። የክርስቶስን ብልጫ በዚህ መልዕክት መናገር ለምን አስፈለገ ለሚለው ጥያቄ ደግሞ መልሱ በወቅቱ ከአይሁዶች የኃይማኖት ክፍሎች መካከል ክርስቶስን መከተል ጀምረው በተለያዩ ችግሮችና የተሳሳቱ ትምህርቶች ወደ ኋላ ለመመለስ ለሚያፍገመግሙ አማኞች ምክርና ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ነው። የአማኝ እድገት**ለራሱና ለሌላው ጥቅም አለው።**

የዕብራውያን መልዕክት ጸኃፊው የተለያዩ መንፈሳዊ ነገሮችን አላደረጋችሁም እያለ ከሚወቅሳቸው ነገሮች አንዱ ያለው በዕብ 5፡12-17 ነው።ይህ ክፍል እንደሚነግረን በጌታ ቢቆዩም ብዙ አለማደጋቸውን ነው። አላደጋችሁም ብሎ የሚላቸው ነገር ደግሞ <u>እጅግ ዋና ነገር ነው</u>። ይኸውም ስለ ክርስቶስ ጥልቅ ትምህርት አለማወቅ ነው። እንደውም ሌሎችን በማስተማር አገልጋዮች መሆን ሲገባቸው እነርሱ ራሳቸው በየዓመቱ ለጋ ትምህርት ፈላጊዎች እንደሆኑ ይናገራል።

ዕብ 5፡11-14 ብቻውን የቆመ ስላልሆነ በምዕራፉ ባለፉት ቁጥሮች ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን የክህነት አገልግሎት የላቀ አገልግሎት ያለው ሆኖ ነገር ግን በምድር ላይ በመከራና በብርቱ ጩኸት እንዴት እንደጸና ይናገራል።  ብርቱ ጩኸቱን እንባውንና ጸሎቱን  አባቱ ሰማው። በተጨማሪም እግዚአብሔር አከበረው። ለሌሎችም የመዳን ምክንያት ሆነ (ዕብ 5፡1-10)። የዕብራውያን መልዕክት ጸኃፊ ይህን የክርስቶስን ህይወትና አገልግሎት ለትምርህታቸው እንዲሆን በጠለቀ መልኩ ለማስተማር ፈልጎ አማኞቹ የመስማት አቅም እንደሌላቸው ይናገራል። መማር የምንፈልገው ምንድ ነው? ፍላጎታችን ለመፈሳዊ ህይወት እድገታችን ወሳኝ ነው። አማኝ የቃሉ ተማሪ ነው።

**ሀ. ለእድገታቸው እንቅፋት ምን ነበረ?**

1. **ጆሮቻችሁም ስለፈዘዙ  ለመማር ዳተኞች ነበሩ  (ዕብ 5፡11)**
   **ዳተኛ ማለት ቸልተኛና ለአንድ ነገር ዋጋ የማይሰጥ ማለት ነው። አማኝ ላመነበት ነገር ራሱን የሚሰጥ መሆን አለበት ነው። ስንፍና ህይወታችንን ያቀጭጫል።** ‘‘ስለእርሱም የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፥ጆሮቻችሁም ስለፈዘዙ በቃል ልንተረጉመው ጭንቅ ነው’’(ዕብ 5፡11)።  እወነተኛ የህይወት ጣዕም ካልገባው የአማኝ ጆሮ ይፈዛል። ሙሉ ባልሆነ ልብ ይከተላል። የሚፈትን ነገር ሲመጣበት እምነቱን ትቶ ለመሄድ ብዙ ጊዜ አይፈጅበትም። በወቅቱ የነበሩ የአይሁድ አማኞች የገጠማቸው ችግር ይህ ነበር። ሌላው ጆሮዎቻችን የሚፈዘው የሚፈልገውን ነገር ብቻ መስማት ሲንፈልግ ነው። የጌታ ቃል እንድንሰማ የሚፈልገውን እንጂ እኔ ሊሰማ የሚፈልገውን መሆን የለበትም። መንፈሳዊ ጥማት እጅግ መሰረታዊ ነገር ነው።

2. **ጠንካራ ምግብ ለመብላት መስጠትና ፍላጎት ማጣት አንዱ እንቅፋት ነው (ዕብ 5፡12)** "ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርትእንዲያስተምራችሁ እንደገና ያስፈልጋችኍልና፤የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም" (ዕብ 5፡12 )። በዕምነታችን እድሜ እየጨመርን ስንሄድ ጠንካራ መንፈሳዊ ምግብ እንድንበላ ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሐዋርያው ጴጥሮስ ለጌታ ቃል ፍላጎት እንዲኖረን ያዘናል። "እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ተንኰልንም ሁሉ ግብዝነትንም ቅንዓትንም ሐሜትንም ሁሉ አስወግዳችሁ፥ ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፥ ለመዳን በእርሱ **እንድታድጉ** አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ"(1ጴጥ2፡1)። ለጌታ ቃል ፍላጎት እንድኖረን ማስወገድ የሚገባንን ነገሮች ማስወገድ አለብን።

3. **ውጤቱ ትክክለኛ የጽድቅ ቃል አለማወቅን ያመጣል (ዕብ 5፡13)** "ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና"። ህጻን ልጅ ጠንካራ ነግሮችን ለማወቅ እንደማይችል መንፈሳዊ ህጻን በመንፈሳዊ እውቀቱ ላይ የሚመጡትን ጠንካራ ትምህርቶችን መመለስ አይችልም። መረዳትም አይችልም።

**ለ. ጠንካራ ምግብ ለመንፈሳዊ ህይወት እድገት ጥቅሙ ምንድ ነው?**

መንፈሳዊ ጠንካራ ምግብ ማለት በጥቅሉ የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮ ሙሉ እውቀት ማግኘት ነው። ማለትም ለምሳሌ ስለ ክርስቶስ መለኮትና ስብዕና፣ ስለ ሥላሴ ትምህርት፣ስለ ኃጢአት፣ ስለ ድነት፣ስለ ዳግም ምጽዓት፣ ስለ ትንሳዔ፣ ስለ ዘላለም ህይወት ወዘተ በቂ እውቀት ማግኘት ነው። ይህ ደግሞ ከስህተት አስተምህሮ ይጠብቀናል። ከመልዕክቱ እንደምንረዳው ሁሉም ባይሆኑ የዕብራውያን መልዕክት ተቀባዮች ስለ ክርስቶስ ሙሉ እውቀት ያላቸው አይመስሉም። እውቀት አለን ብሉ እንኳን ያንን እውቀት መተግበር የቻሉ አይደሉም።
ስለዚህ በክፍሉ መሰረት በአጭሩ መንፈሳዊ ጠንካራ ምግብ መመገብ

- መልካሙን ከክፉ ለመለየት ይጠቅማል (5፡14ሀ) ። የስህተት ትምህርትና ሌሎችም መንፈሳዊ ችግሮች ቢከሰቱ…
- ፍጹም ያደርጋል፣ብስለትን ይሰጣል (5፡14ሀ)። ስለዚህም በትምህርት ነፋስ መፍገምገም አይኖርም። ከተለያዩ የስህተት ትምህርቶች እንጠበቃለን። "ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹ ማን ሰዎች ነው" (ዕብ 5፡14)።
- **ጠንካራ ምግብ መመገብ ለሌሎች እንድንተርፍ ይረዳናል (አማኝ አገልጋይ ነው)**

ማብራሪያ እንዲሆነን በሐዋርያት ሥራ 18፡24-28 ስለ ተጠቀሰው አገልጋይ ስለ አጵሎስ ሲናገር እርሱ የመጽሐፍት እውቀት እንደነበረውና ለሌሎችም ይገልጥ እንደ ነበር ያስረዳል። ስለዚህ ለራሳችንና ለሌሎችም ለማስተማር የመጽሐፍት እውቀት መኖር አንዱ የእድገት መለኪያ ነው። ስለ አጵሎስ እንዲህ ይላል "በወገኑም የእስክንድርያ ሰው የሆነ ነገር አዋቂ የነበረ አጵሎስ የሚሉት አንድ አይሁዳዊ ሰው ወደ ኤፌሶን ወረደ፤እርሱም በመጻሕፍት እውቀት የበረታ ነበረ።25 እርሱ የጌታን መንገድ የተማረ ነበረ፥የዮሐንስንም ጥምቀት ብቻ አውቆ በመንፈስ ሲቃጠል ስለ ኢየሱስ ይናገርና በትክክልያ ስተምር ነበር።26 እርሱም በምኵራብ ገልጦ ይናገር ጀመር። ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ፥ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል ገለጡለት።27 እርሱም ወደ አካይያ ማለፍ በፈቀደ ጊዜ፥ወንድሞቹ አጸናኑት፥ይቀበሉትም ዘንድ ወደ ደቀ መዛሙርት ጻፉለት፤በደረሰም ጊዜ አምነው የነበሩትን በጸጋ እጅግ ይጠቅማቸው ነበር፤28 ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ከመጻሕፍት እየገለጠ ለአይሁድ በሁሉ ፊት በጽኑ ያስረዳቸው ነበርና" (18፡24-28)። ይህ የአጵሎስ ህይወትና አገልግሎት ከአማኝ ሁሉ ይፈለጋል። ጌታ በእውቀት ይሙላን።

ቢሆንም ለእርሱም ትምህርት ያስፈልገው ነበረና ጵርስቅላና አቂላ ያስተምሩት ነበር። እርስ በእርስ በትህትና መረዳዳት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የዕብራውያን መልዕክት ተቀባዮች እንዳያድጉ ያደረጋቸው ችግር ምንድ ነበር? (ወደ ኋላ እንዲያፍገመግሙ ያደረገው ነገር)
2. የዕብራውያን መልዕክት ዋና ሀሳብ "ክርስቶስ" እርሱና አገልግሎቱ ይበልጣል ነው? ክርስቶስ ማንነቱና አገልግሎቱ ስለ መብለጥ መናገር ለእነርሱ ምን ይጠቅማል?
3. ዕብ 5፡11-12 ዋናው ችግራቸው ምንድ ነው? ዳተኛ ማለት ምን ማለት ነው? ከዚህ ዘመን አማኞች ጋር የሚገናኝ ነገር አለ?
4. በዕብ 5፡11-12 ውስጥ የተጠቀሰው "ወተት" ምንድ ነው?
5. እንደዚሁም መንፈሳዊ "ጠንካራ ምግብ" ተብሎ የሚጠራው ምንን ነው? ምሳሌ ጥቀሱ።
6. ሐዋርያው ጴጥሮስ ለማደግ አስወግዱ የሚላቸው ነገሮች ምንድ ናቸው (1ጴጥ 2፡1)
7. ለሥጋም ይሁን ለመንፈሳዊ ህይወት ጠንካራ ምግብ ጥቅሙ ምንድ ነው?
8. የሐዋ 18፡24-28 በማንበብ አጵሎስ ምን ዓይነት አማኝ እንደነበረ ይናገራል? ከአጵሎስ ሕይወት ምን እንማራለን?
9. የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ምንድ ነው? በዓላማውም መሠረት አጠቃላይ ከዛሬ ጥናት ምን ተማርን?

**መደምደሚያ**

አማኝ ዳግም ከተወለደ ቀን ጀምሮ ማደግ አለበት። አለማደግ ማንንም አያስደስትም። ማደግ ወይም መለወጥ የተፈጥሮ ህግ ነው። አለማደግ ለራስም ይሁን ለክርስቶስ አካል እንቅፋት ነው። ወተት ከመጠጣት አልፈን ጠንካራ ምግብ መመገብ አለብን። አለማደግ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባትም እንቅፋት ሊሆን ይችላል። ለማደግ ማንበብ፣መስማትና መማር!መማር!መማር! አለብን። በማደግ ለሚጠይቁን ሁሉ መልስ ለመስጠት መዘጋጀት አለብን።

ትህትና የተሞላ ማሳሰብያ፦ ለሚቀጥለው ጥናት 1ቆሮ 1-3 እንዲታነቡ በትህትና እንጠይቃለን

## ማደግ
## ጥናት 3

**የምንባብ ክፍል 1 ቆሮ 1-3፣ (በተለይም ለዕለቱ ጥናት 1ቆሮ 1፡9-12፣ 1ቆሮ 2፡6-16፣3፡1-7 ቢነበብ ጥሩ ይሆናል)**

**በቆሮንቶስ ቤ/ክ የተከሰተው ችግር በመንፈሳዊ እውቀት ያለ ማደግ ውጤት**

**ዓላማ**

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በትክክለኛ በእግዚአብሔር ቃል እውቀት አለማደግ ስለሚያመጣው አሉታዊ ውጤትና መፍቴሔዎች ይሆናል።

**መግቢያ**

የቆሮንቶስ አማኞች አለማደጋቸው በምን ተገለጠ? አማኞቹ ክርስቶስን ሳይሆን ወደ ክርስቶስ መንገድ ያሳዩአቸውን ሰዎች ማየት ስለጀመሩ መከፋፈል በመካከላቸው ተከሰተ። ይህም ደግሞ ሥጋዊ ወይም ያላደጉ አማኞች እንደሆኑ ምልክት ነው (1ቆሮ 1፡10-12፣2፡1-3 እባክዎን ይህ ክፍል ይነበብ)።

በብዙ አብያተ ክርስቲያናት አለመግባባት ሲፈጠር አማኞች ምንም እንኳን አገልጋዮች ስህተት ቢሰሩም ባይሰሩም በጭፍን እውነት ያለውን ክርስቶስን ሳይሆን መሪዎችን ወይም ሌሎች አገልጋዮችን መከተል ይጀምራሉ። ውጤቱም ደግሞ ለራስ ችግር ውስጥ ከመግባት አልፎ ወንጌል እንደ ሚገባ እንዳይሮጥ ማደናቀፍ ይሆናል። የቆሮንቶስ አማኞች ለዳኑት ወንጌል ሙሉ እውቀት ስላልነበራቸው የተለያዩ ስህተቶች ውስጥ ገብተዋል። ከላይ የተጠቀሰው ችግር አንዱ ነበር። በ1ቆሮ 1፡10-4፡21 የተጠቀሰው መከፋፈል አንዱ ችግር ነበር።ክርስቶስን ሳይሆን በውስጣቸው የሳሉት የሰበኩላቸውን አገልጋዮችን ብቻ ነበር።እውነተኛ እውቀትና መንፈስዊ እድገት ያለው አማኝ "እኔ የጳውሎስ ነኝ፥እኔስ የአጵሎስ ነኝ፥እኔ ግን የኬፋ ነኝ" (1ቆሮ 1፡12) አይልም። ዓይናችንን የጣልነው ያስተማሩንን፣ ያጠመቁንንና ፍቅር ያሳዩንን ሊሆን ይችላል። ይህንን ማድረግ በራሱ ስህተት አይደለም ችግሩ እምነታችን ሲፈተን ለተፈተንበት ነገር በምንሰጠው መልስ እድገታችን ይታወቃል።ውጤቱም አካሉን ወይንም ቤተ ክርስቲያንን መክፈል ብቻ ሳይሆን <u>**ተመልሰው ደቀመዝሙር ካልሆኑ**</u> የራሳቸውንም ህይወት ችግር ውስጥ ማስገባት ይሆናል። ሁል ጊዜ ክርስቶስን የመምሰል እድል አያልቅም። አሁንም በህይወት እስካለን ድረስ እድሉ እንደተከፈተ ነው።

**ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ችግር ራሳችንን ለመከልከል ምን እናድርግ?**

1. አገልጋዮችን ሳይሆን ያዳነን ክርስቶስን ማየት
    - "ስለዚህ፥ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፥ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤" (ዕብ 3፡1)
2. እንደ ጌታ ተከታይ በዓለም ላይ ካሉት ወይም ካላመኑት ልዩነት እንዳለን ማወቅ
3. መከፋፈል ለክርስቶስ አካል እድገት እንቅፋት እንደሆነ ማወቅ
4. መከፋፈል ወንጌልን ለማድረስ አስቸጋሪ እንደሆነ ማወቅ
5. የክርስቶስን አካል መከፋፈል ተጠያቂነትን እነደሚያመጣ መገንዘብ

6. *ሥጋዊ አማኝ አለመሆን፦* "እኔም፥ወንድሞች ሆይ፥የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥በክርስቶስም ሕፃናትእንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደመሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም። 2 ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤ 3 ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?(1ቆሮ 3፡ 1-3)። ስለዚህ ከእንደዚህ ዓይነት መንፈሳዊ ልጅነት መጠንቀቅ

7. ሐዋርያ ጳውሎስ በቆላስይስ መልዕክት "ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታነጹ፥እንደተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ፥ምስጋናም ይብዛላችሁ" (ቆላ 2፥7)ይላል። ስለዚህ በክርስትና እንደ ዘንባባ ዛፍ ሥር ካልሰደድን በተለያዩ ፈተናዎች እንወድቃለን። ሥር የምንሰደው በመማርና በማንበብ ነው።

8. በመጨረሻም የሐዋርያ ጴጥሮስን ምክር መስማት "ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ **<u>ጸጋና እውቀት እደጉ</u>**" (2ኛየጴጥ 3፡18)። በመንፈሳዊ ህይወት ለማደግ የክርስቶስ እውቀት ያስፈልገናል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. 1ኛ ቆሮ 1፡9-10 ከ1ቆሮ 1፡11-12 ጋር ምን ይገናኛል? በዚህ ክፍል መሰረት የአማኞቹ ዋና ችግራቸው ምንድ ነው?
2. በቆሮንቶስ ቤ/ክ የነበሩ አማኞች ማድረግ የነበረባቸው ነገር ምን ነበር?
3. በ1ኛ ቆሮ 2፡6-16 መሰረት ስንት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ ይናገራል? በተለይም ቁ.6 ምንን ያመለክታል?
4. 1ኛ ቆሮ 3፡1-3 ሐዋርያው ጳውሎስ እየወቀሳቸው ያለው ለምንድ ነው?
    - በዚህስ ክፍል መሰረት የቆሮንቶስ አማኞች ሥጋውያን የመሆናቸው ምልክት ምንድ ነው?
5. ጽኑ መብል ምንድ ነው? የቆሮንቶስ አማኞች ጽኑ መብል መብላት ያቃታቸው ምክንያት ምንድ ነው?

**<u>ከዚህ በታች ያለውን ክፍል በሚቀጥለው ቀን ማጥናት ትችላላችሁ</u>**

6. አማኝ ካላደገ የክርስቶስን አካል ሊከፋፍል ይችላል ማለት ነው? እንዴት?
7. ሐዋርያው ጳውሎስ ያሳደጉንን አገልጋዮች ምንም ቦታ አትስጡ ነው እያለ ያለው? ካልሆነ ምንድ ነው?
8. የሚከተለው ጥቅስ ከላይ እያጠናን ከመጣነው ጋር ምን ይገናኛል? "ወንድሞች ሆይ፥ እኔን የምትመስሉ ሁኑ፥ እኛም እንደ ምሳሌ እንደምንሆንላችሁ፥ እንዲሁ የሚመላለሱትን ተመልከቱ" (ፊል 3፡17)።
9. 2ኛ ጴጥ 3፡18 እና ቆላ 2፥7 ከዚህ ጥናት ጋር ምን ይገናኛል? ሐዋርያው ጴጥሮስስ ምን ምክር ይሰጠናል?
10. ይህ ጥናት ሊያስተምረን የፈለገው ነገር ምንድ ነው? በመንፈሳዊ ህይወት ማደግ ከዚህ ክፍል ጋር ምን ይገናኛል?

***መደምደሚያ***

ክርስትና እውቀት ነው። ይህ እውቀት ደግሞ የሚገኘው በእምነት የጌታን ቃል በማጥናትና በቅንነት በመማር ነው። አንድ አማኝ በጌታ ከዳነ በኋላ መሠረቱ ክርስቶስ መሆን አለበት። ሥጋዊ አማኝ ሆኖ መቆየት የለበትም። በሩን ለዓለም፤ ለሠይጣንና ለሥጋዊ ምኞቶች አሳልፎ መስጠት የለበትም። በጌታ ትምህርት ያሳደጉን ሰዎች ቢሳሳቱ መሳሳት የለብንም።

**ማደግ**

**ጥናት 4**

**ሚዛንየጠበቀ መንፈሳዊ እድገት**

**የምንባብ ክፍል 1ጢሞ 4፡15፣ሉቃ 2፡52 ፣ቆላ 2፡16-3፡1**

**ዓላማ፡-** አማኝ ሚዛን የጠበቀ ህይወት መኖር እንዳለበት ማሳሰብና መንገዱንም ማሳየት

**መግቢያ፡-**

ብዙ ጊዜ ህይወታችን በአንድ መንገድ የቀናለት ይሆንና በሌላ ደግሞ ሳይሳካ ይቀራል። የጌታ ቃል ግን በሁለንተና እንድናድግና እንዲቀናልን ይፈልጋል ይጠይቀናልም። "ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግነበር" (ሉቃስ 2፥52)። ይህ ክፍል ጌታ ኢየሱስ በሁለንተና እንዳደገ አማኝ። እድገቱም በሰውና በጌታ ፊት ያድግ ነበር። በሐዋርያው ጳውሎስ መል" 11-12 ይህን እዘዝና አስተምር። በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ምሳሌ ሁን እንጂ፥ ማንም ታናሽነትህን አይናቀው። 13 እስከመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ። 14 በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፥ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታችል አትበል። 15 **ማደግህ በነገር ሁሉ** እንዲገለጥ ይህን አስብ፥ይህንም አዘውትር። 16 ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ይህን ብታደርግ፥ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና" (1 ጢሞ 4፡11-16)። ነገር ሁሉ ማለት ምን ማለት ነው። ነገር ሁሉ ንግግርና ተግባርን ይመለከታል።

"11 እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤12-13 ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና **በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥** የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።14 እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት አይገባንም፥15 ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤16 ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል" (ኤፌ 4፡12-16)።

**ሚዛን የጠበቀ ህይወት ሌሎችን ማለትም የክርስቶስን አካል ማሳደግ ይጠበቅብናል።**

**በሁሉም አቅጣጫ ማደግ ማለት ምን ማለትነው?**

1. **በጌታቃል እውቀት ማደግ ማለት ነው፡-** የምናደርገውን ሁሉ በሙሉ እውቀት ማድረግ እንድንችል ያደርጋል። በተጨማሪም በቃሉ እውቀት ማደግ ከተለያዩ ስህተቶች ይጠብቀናል። በዚህ ዘመን ካሉ ከተለያዩ ችግሮች እንጠበቃለን።

    "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ" (ቆላ 3፥16)።

2. **ከጌታጋር በጸሎት ህብረት ማድረግ ነው፡-**

    ሚዛን የጠበቀ መንፈሳዊ ህይወት መኖር አንድ ልጅ በሙሉ ጤንነት ሂደት እንደሚያድግ ይቆጠራል። በተጨማሪም አንድ ዛፍ በተፈጥሮው ለዛፉ እንደተሰጠው በቁመት የሚጨምር ከሆነ በቁመት ማደግ ወይም ደግሞ ወደ ጎንም የሚያድግ

ከሆነም ደግሞ ወደ ጎን ካላደገ እናም ፍሬም ካላፈራ እንደሚፈለገው ውጤታማ ሊሆን አይችልም። ገበሬውም አይደሰትም። እምነትም በእድገት ሙሉ እንዲሆን ጸሎት አንዱ ነገር ሊሆን ይገባል።

በተጨማሪ ለሌሎች በጸሎት መጋደል አንዱ የማደግ ምልክት ነው። አማኝ ሁሉ የክህነት አገልግሎት ማገልገል አለበት "ከእናንተ የሆነ የክርስቶስ ባሪያ ኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብላችኋል። በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ተረድታችሁና ፍጹማን ሆናችሁ እንድትቆሙ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ በጸሎቱ ይጋደላል" (ቆላ 4፡12)።ጸሎት ጥሩ ነው ማለት ብቻ ሳይሆን መጸለይ ነው።

3. **በተጨማሪም** ሚዛን የጠበቀ ህይወት መኖር ማለት ለሚጠይቁን **መልስ ለመስጠት መዘጋጀትና ከስህተት ትምህርት ራስን መጠበቅና መቀደስ ነው (1ኛጴጥ 3፥15 እና ቆላ 2፡16-3፡1)።**

አማኝ በእምነቱ ለሚነሳበት ጥያቄዎች ሁሉ ከጌታ ቃል በማንበብና በመማር በትህትናና በየዋህነት መልስ ለመመለስ ዝግጁ ሊሆን ይገባል። "…ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን" (1ኛጴጥ 3፥15) ። የያዝነው እምነት እውነተኛ እንደሆነ እርግጠኞች ልንሆን ይገባል። በዚህ ምድር የተለያዩ የኃይማኖት ድርጅቶች የሚያደርጉት ልምዶች በእግዚአብሔር ቃል እይታ ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ማስረጃ ሊኖረን ይገባል። አንድ የሌላ ኃይማኖት ተከታይ ሰው ጥያቄ ከጠየቀን ከመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ልንሰጥ ያስፈልጋል። ይህ እኛንም የሚሰሙንንም ከስህተት ይጠብቀናል። ለዚህም ማንበብ!ማንበብ!ማንበብ! እናም መማር!መማር!መማር! አማራጭ የለውም። በዚህ ጥቅስ ስለተጠቀሱ ነገሮች ብንጠየቅ መልሳችን ምንድ ነው? በትህትና መንገር የምንፈልገው ይህ ጥናት ስለ እነዚህ ነገሮች ማስተማሪያ ጥናት እንዳልሆነ ነው። ነገር ግን ቤ/ክ በተለያዩ ጊዜያት ታስተምራለች። በዚህ ጥናት ስለ እነዚህ ነገሮች አንስተን በጥልቀት መነጋገሩም ተገቢ አይሆንም።

4. ***ቃሉን ማድረግ (ያዕቆብ 1፥22-23)***

ስለ ጦርነት ትምህርት ማስተማርና ሄዶ እየተዋጉ ማሳየት ልዩነት አለው። ጌታ በህይወቱ በሥራ ወይም በተግባር ያሳይ ነበር። "ልጆቼ ሆይ፥በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ" (1ኛየዮሐ3፥18)።

"ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ።ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤" **(የያዕቆብ 1፥22-23)። ከላይ ስላነበብናቸውና የተማርናቸውን ሥራ ላይ ካላዋልን ዋጋ አይኖረውም። ቃሉን ማንበብ ጥሩ እንደሆነ መናገር ብቻ ሳይሆን ማንበብና ሥራ ላይ ለማዋል እጅግ ጥረት ማድረግ ወሳኝ ነው።**

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. አንድ ህጻን ልጅ በዕድገቱ ሂደት እንደሚገባ ካልተንከባከቡት ሚዛን ጠብቆ አያድግም። ይህ ምሳሌ ከመንፈሳዊ ህይወት ጋር ምን ይገናኛል? ማብራሪያ? ህጻኑ ከተወሰነ ዓመታት በኋላ ምን ኃላፊነት አለብት (ሙብላት በሚችልበት እድሜ ሲደርስ)?
2. በ1ኛ ጢሞ 4፡15 "በነገር ሁሉ" የሚለውን ቃል አብራሩ። በነገር ሁሉ ማደግ ማለት ምን ማለት ነው?
3. "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ" (ቆላ 3፥16) ። በጌታ ቃል እውቀት ለማደግ ምን እናድርግ? አሁን ምን ምን እያደረግን ነው?
4. "ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር" (ሉቃስ 2፥52) ይህ ቃል አማኝ ሚዛን የጠበቀ ህይወት እንዲኖረው ምን ያስተምራል?
5. በቆላ 2፡16-3፡1 ሚዛን የጠበቀ ህይወት ስለ መኖር ምን ያስተምረናል?

6. የተለያዩ የኃይማኖት ድርጅቶች ስለ ልምዳቸው እውነተኝነት ቢጠይቁን መልስ ለመመለስ ዝግጁ መሆን የማን ኃላፊነት ነው? እወቀቱን እንዴት ማግኘት እንችላለን?
7. ምስክርነት፡- ከተለያዩ የኃይማኖት ድርጅቶች እንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ገጥሞን ያውቃል? አካፍሉ። ምን አደረጋችሁ? ከዚህ በኋላስ ምን እናድርግ?
8. የያዕቆብ 1፥22-23 ከዚህ ጥናት ጋር ምን ይገናኛል? ተወያዩ
9. ሚዛን የጠበቀ ህይወት ማለት ምን ማለት ነው?
10. በህይወትህ (ሽ) ምን የጎደለ ነገር ያለ ይመስልሃል? ነጻነት ከተሰማችሁ አካፍሉ? ዛሬ ምን ወሰንክ (ሽ)?
11. ይህ ጥናት ሚዛን የጠበቀ ህይወት ስለመኖር ምን አስተማረ? ተወያዩ።

***መደምደሚያ***

ለአማኝ በሁሉም የህይወት አቅጣጫዎች ማደግ እጅግ ጠቃሚ ነው። አማኝ በጸሎት፣ከሌሎች ጋር ባለው ህብረትና በእውነተኛ ፍቅር፣በወንጌል ስብከት፣ ቃሉን በማንበብ፣ራስንና ሌሎችን ከስህተት ትምህርት በመጠበቅ ማደግ በጌታ ቤት ጸንቶ ለመቆየት <u>እጅግ መሰረታዊ</u> ነገር ነው።

**ክፍል አራት**
**እንሂድ**
**ጥናት አንድ**

**የወንጌል ጥሪን ለመወጣት እንያያዝ**

**ዓላማ፡-** የወንጌል ተልዕኮ የጋራ ጥሪ መሆኑን በመገንዘብ አደራችንን ለመወጣት እንድንያያዝ ማሳሰብ።

**መግቢያ**

የወንጌል ጉዳይ ከአዳም ውድቀት ጀምሮ ሰዎችን በሚፈልግ እና በሚያፈቅር ጌታ ልብ ያለ፣ የነበርና አሁን ደግም ለኛ የተሰጠን አደራ ነው። ሆኖም ይህ ወንጌል በአንድነት፣ እጅ ለጅ ተያይዘን የምንወጣው ታላቅ አደራ እንጂ ጥሪው ለተወሰኑ ወገኖች (ማለትም ለወንጌላዊያን ወይም በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ለተሰማሩ) ብቻ ሳይሁን ለአማኝ ሁሉ የተሰጠ አይደለም። አደራው ለአማኞች በሙሉ የተሰጠ እንደመሆኑ ኃላፊነቱን በተሳካ ሁኔታ ለመወጣት የአላማ አንድነት እና የልብ መያያዝ ያስፈልጋል።

እንግዲህ በዛሬው ጥናታችን እያንዳንዳችን በነፍስ ወከፍ በዚህ የወንጌል አደራ ውስጥ ድርሻ እንዳለን በመረዳት ይህንን አደራ ከግብ ለማድረስ እርስ በእርስ መተባበር እና መያያዝ እንዳለብን እንመለከታለን።

በመጀመሪያ ወንጌልን ለሰዎች ሁሉ የማድረስ ጉዳይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንገብጋቢ እና አቸኳይ ነገር እንደሆነ ከቃሉ የምንገነዘበው እውነት ነው። ጉዳዩ እግዚአብሔር ራሱ ችላ የማይለው ነገር በመሆኑ የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀበት ጊዜ አንስቶ የጠፋውን ሰው በወንጌልን እንደሚያድነው ራሱ እግዚአብሔር ደጋግሞ ተናግሯል (ዘፍ 3፡15፤ ገላ 3፡8)። ልጁም ክርስቶስ ኢየሱስ ክብሩን ትቶ እንዲወርድ፣ በመስቀል እንዲንገላታ ያደረገውም፣ ይኼንኑ የጠፋውን ሰው ፍለጋ ነው። ‘‘የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግ እና ሊያድን መጥቶአልና’’ (ሉቃ 19፡10፣ ማቴ 19፡11)። የወንጌል ነገር በጌታ ሞት ብቻ ሳያበቃ፣ ሐዋሪያቱ እና ደቀመዛሙርቱም ይህንን ምስራች ለጠፋው ሰው በየደረሱበት እንዲያበስሩ ኃላፊነት ተሰቷቸዋል (ማር 16፡15፤ ሉቃ 10፡1-17)። ሆኖም የነገሩን ክብደት እና ጥልቀት ዋጋ የሚሰጠው በመሆኑ፣ ሐዋሪያት እና ደቀመዛሙት ቢያስፈልግ ነፍሳቸውን እስከመስጠት ድረስ በመታመን ወንጌልን መስክረዋል።

ሆኖም እንድናስተውል የሚገባን ነገር፣ ይህ የወንጌል አደራ ለጥንቷ ቤተክርስቲያን ወይንም ለሐዋሪያት ወይንም ዛሬ በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ለተሰማሩ ብቻ የተሰጠ ሳይሆን የጌታ ብርሃን ለበራለት ምድረ አማኝ ሁሉ የተሰጠ አደራ ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ይህንን እውነት ሲያስምር ‘‘እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁ የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ … ናችሁ’’ (1ኛ ጴጥ 2፡9) ሲል አማኞች በሙሉ ድነትን የተቀበልነው ወንጌልን ከማብሰር ሃላፊነት ጋር እንደሆነ ያሳስበናል። ለዚህም ነው ጌታ ደቀመዛሙርቱን ሲጠራቸው፣ ለራሳቸው ድነት እንዲቀበሉ ብቻ ሳይሆን ወንጌልንም እንዲያዳርሱ ጭምር እንደነበር ቅዱስ ቃሉ የሚያሳየን (ለዚህ በማር 3፡13 ላይ ያለውን ያገናዝቡ)። ለዚህም ነው ይህ እውነት የገባቸው የፊልጵስዩስ ቤተክርስቲያን አማኞች ድነትን ሲያገኙ፣ የተቀበሉትን ምስራች ለሌሎችም ወዲያው ማካፈል የጀመሩት (ፊል 1፡3-6)።

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው ወንጌልን ለጠፋው ሰው ማዳረስ አንገብጋቢ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ ለእያንዳንዱ አማኝ የተሰጠ ሃላፊነት ነው። በዚህ መሰረት አቅማችን በሚፈቅደው መጠን በግል የምስራቹን ማዳረስ ጥፋት ባይሆንም፣ ‘‘ድር ቢያብር አንበሳ ያስር’’ እንዲሉ በአንድ ልብ በመያያዝ እና በሕብረት መዝመት ግን አይነተኛ ለውጥ የሚያመጣ በመሆኑ አማኞች ለዚህ አላማ ልንያያዝ ያስፈልጋል። በአንድነት ተያይዞ ወንጌልን ለማዳረስ መነሳት የሚቻልባቸው ብዙ ነጥቦች ሊኖሩ ቢችሉም፣ ለዚህ ጥናት እንዲያመቸን ወንጌል እንደሚገባ እንዲሮጥ ልንያያዝባቸ የሚገቡ አራት ነጥቦችን እናያለን።

1. **በአንድ ልብ ለወንጌል እንደሚገባ መኖር**

እያንዳንዳችን በግል ሕይወታችንም ሆነ በማሕበራዊ ኑሮአችን የምንኖረው ሕይወት በወንጌል ሩጫ ላይ ታላቅ ተጽዕኖ ያመጣል። ወንጌልን ለሌሎችም ስናዳርስ እርስ በእርስ የምንያያዝበት እና ለአንድ አላማ የምንቆምበት አንደኛው መንገድ ሕይወታችንን እንደ ወንጌሉ እውነት ማስተካከል ነው። በአንድ በኩል ወንጌል ይለውጣል ብለን እኛ ግን ሕይወታችን ካልተለወጠ ወንጌሉን ፉርሽ እናደርገዋለን። በሌላ በኩል ወንጌላዊው በወንጌል ስርጭቱ፣ ሰባኪው በስብከቱ፣ አስተማሪውም በአስተምህሮቱ ያስተላለፉትን እውነት እኛ ደግሞ በሕይወታችን ኖረን በማሳየት በአንድ ልብ ከሰራን ወንጌል በሚገባ ይሮጣል። ሆኖም ግን አንዱ ያስተማረውን፣ እኛ ደግሞ በአረማመዳችን ካፈረስነው የመያያዝ እና የልብ አንድነት ጎድሏል ማለት ነው። ስለዚህም በአካሄዳችን እና በአመላለሳችን፣ እርስ በእርስ ልንያያዝ ይገባል።

ከዚህም ባሻገር በፊል 1፡27- 28 እንዲሁም ፊል 2፡14-16 የተጻፈውን ስንመለከት በክርስትና አካሄዳችን በአንድ ልብ ተያይዘን ወንጌልን ማሮጥ እናዳለብን ያስገነዝቡናል። በነዚህ ክፍሎች መሰረት

- በአንድ ልብ ለወንጌል እንድንጋደል
- ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ እንድንኖር
- በመጥፎ እና በጠማማ ትውልድ መካከል በመልካም ሕይወት እንድንመላለስ
- የሌላውን ድካም እና ሩጫ ከንቱ በማያደርግ አካሄድ እንድንመላለስ ያሳስቡናል።

## 2. በቅዱሳን ሕብረት ውስጥ በአንድ ልብ በመትጋት

የእግዚአብሔር አሰራር ልዩ ልዩ እንደመሆኑ፣ አንዳንዶችን ለስራው እንደነ ኢሳያስ እና ጳውሎስ በግል ሲጠራ (ኢሳ 6፡8፣ ሐዋ 9፤ 26፡19-18) ሌላ ጊዜ ደግሞ በቅዱሳን ሕብረት እና አንድነት ውስጥ ለራሱ ስራ ይለያል (ሐዋ 13፡1-3፣ 47-49)። እንግዲያ እግዚአብሔር በቅዱሳን ሕብረት ደስ ከተሰኘ፣ በእንደዚህ አይነት ህብረት ውስጥ ሰወችን ለስራው የሚለይ ከሆነ፣ የቅዱሳን ሕብረት እና ጸሎት ዘወትር የምንተጋበት ነገር እንዲሆን ይገባል (ፊል 4፡1-3፣ 15፤ 1ኛ ጢሞ 2፡1-7)። እንዲህ አይነቱ ሕብረት ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ መድረክ ከመፍጠሩ ባሻገር፣ ለወንጌል ሥራ እርስ በእርስ እንድያያዝ፣ በአንድ ልብ እንድንጸልይ እንዲሁም ስለወንጌል ሥራ እንድመካከር እድል ይሰጠናል። ስለዚህ ለዚህ ቁልፍ በሆነውን የቅዱሳን ኅብረት፣ ጸሎትና ትብብር ዘወትር እንትጋ።

## 3. ወንጌልን ማዕከል በማድረግ በተሰጠን ፀጋ ማገልገል

ከላይ እንደገለጽነው ወንጌልን ለሌሎስ ማደረስ ለጥቂት አገልጋዮች የተተወ ጉዳይ ሳይሆን ለሁላችም የተሰጠ አደራ ነው። ሆኖም ግን፣ ይህ ማለት ሁላችም ለሙሉ ጊዜ የወንጌል ሰባኪነት ተጠርተናል ማለት እንዳይደለ ልናስተውል ይገባል። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሁሉም የተለያየ ጸጋ እና የአገልግሎት ድርሻ ሰጥቶአል (1ኛ ቆሮ 12፡4-11፣ ኤፌ 4፡11)። እግዚአብሔር የተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎችን እና የተለያዩ ጸጋ ያላቸው ሰዎችን የሰጠበት አንደኛው ምክኒያት "ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመን እና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት" እንድንደርስ ነው (ኤፌ 4፡12-13)።

እንግዲህ የተለያየ ጸጋ እና አገልግሎት መሰጠቱ ሰወች ክርስቶስን እንዲያውቁ እና ወደ ድነት እንዲደርሱ ከሆነ፣ እኛም ጸጋችንን ለዚሁ አላማ ልንናውለው ይገባል። እንዲያስተምር የተሰጠው፣ ወንጌልን ያስተምር፣ እንዲሰብክ የተሰጠው ወንጌልን ይስበክ፣ የመስጠት ስጦታ ያለው፣ ለወንጌል ስራ በልቡ ጌታ ያሳሰበውን ይስጥ፣ የሚጸልየውም ስላልዳኑት አጥብቆ ይጸልይ፣ እንዲሁም ትንቢት የሚናገረውና በልሳን የሚጸልየው የማያምን ሰው እንዳይሰናከል እና ይበልጥ እንዳይሸሽ ጸጋውን በጥንቃቄ ይጠቀም (1ኛ ቆሮ 14፡23)። ባጭሩ ሁሉም ወንጌልን ማዕከል በማድረግ በተሰጠው ጸጋ ያገልግል።

## 4. ለወንጌል ሥራ የገንዘብም ሆነ የጉልበት ድጋፍ በመስጠት

በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እንደ ጳውሎስ የወንጌል ሰባኪነት ጥሪ የደረሰባቸው ከቦታ ቦታ፣ ከአገር ወደ አገር እየዞሩ እና እየደከሙ ቃሉን እንዲያሰራጩ ቤተክርስቲያን ስትልክ (2ኛ ቆሮ 15-20)፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የነበሩም

ምእመናን ደግሞ በጸሎት እና በገንዘባቸው መደገፍ ልማዳቸው ነበር (ሮሜ 15፡23-30)። በዚህም በቃሉ አገልጋዩች እና በሌላው ምእመን መካከል አንድነት እና መያያዝ የነበረ መሆኑን እንረዳለን።

ይህ እውነት የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብቻ ሳይሆን ዛሬም ቤተክርስቲያ ልትሰራበት የሚገባት መንገድ ነው። ጥሪ ያላቸውን ሰዎች ማወቅ እና መጥራት እና የማሰማራት ሃላፊነት ቤተክርቲያን ያለባት ሲሆን፣ ጥሪው ያለበት ግለሰብ ደግሞ ራሱን በመስጠት፣ ሌላው ደግሞ በገንዘብ (2ኛ ቆሮ 8፡1-4፣ 8) እና በሌላ በሚችለው አቅም ሁሉ ድጋፍ እንዲሰጥ ይገባል። በዚህም ሁላችን ለአንድ አላማ ልንሰለፍ እና ልንያያዝ እንችላለን።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. ታላቁ ተልዕኮ ለተለዩ ወገኖች ብቻ የተሰጠ አለመሆኑን እንዴት ታስረዳለህ?
2. በማርቆስ 3፡13 መሰረት ጌታ ደቀመዛሙርቱን ለምን ነው የጠራቸው?
3. በጴጥሮስ 2:9 አማኞች ከምን ውስጥ ነው የወጡት ለምንስ ጉዳይ? ይህ እያንዳንዳችን ስተሰጠን አደራ ምን ያመለክታል?
4. በፊል 1፡3-6 ስለጥሪያችን ስኬትና ኃይል ምንድን ነው የተጠቀሰው? ይህስ ምን ያመለክትሃል?
5. በፊል 1፡27-28፥ 2፡14-17 የተዘረዘሩት ነጥቦችን ተወያዩባቸው።
    - ‘‘በአንድ ልብ ስለወንጌል መጋደል’’ ምን ማለት ነው?
    - ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ መኖር የሚለው አባባል ምንን ያመለክታል?
6. በፊል 2፡14-17 መሰረት
    - ዘመኑን እንዴት አድርጎ ነው የሚገልጸው?
    - የራሳችንን አካሄድ አስመልክቶ ምን ምክር ይሰጣል?
    - ከነዚህ አሳቦች አኳያ በሌላው አገልግሎት ላይ ስላለው ተጽዕኖና አስትዋጽዎች ምን ትረዳለህ?

   ቁልፍ አሳቦች፦
    - ያለነቀፋ፥ በየዋህነት፥ ያለማንጎራጎር፥ ያለክፉ አሳብ በመሆን፥ እንደ ብርሃን ልጆች፥ ትምክህት ስለመሆን
7. በሚከተሉት ጥቅሶች ላይ በማተኮር ለወንጌል ስለሚለዩ ወገኖችና ስለቅዱሳን ኅብረት ተወያይበት። ሐዋ 13፡1-3፣47-49 ፥ኢሳያስ 6:8
    - የቅዱሳን ጉባኤ በምን መንፈስ ሆነው ሳለ ነው ጥሪው የመጣው?
8. ጥሪውን ከተቀበሉ በኋላ ስላለ መሰጠት ከሐዋ 20፡24-27 ምን ትማራለህ?
9. አገልጋዩን በማገዝ ረገድስ? ፊልጵስዩስ 4፡3, 15
10. በሌላ ክል ለሚከናወን የወንጌል ሥራ እገዛን በማድረግ ረገድ ከ2ቆሮ 8፡1-4፣ 8፥15-20 ምን እንማራለን?
    - የገንዘብ እርዳታን ማድረግ
    - ጽጋን የሚያካፍሉን በመላክ ማገዝ

**መደምደሚያ**

የወንጌል አገልግሎት ለአማኞች ሁሉ የጠፉትን የመመለስና የማስታርቅ አደራ ነው። ሆኖም ግን በጸና የመንፈስ አንድነት እና መያያዝ የምንሰማራበት ታላቅ ሥራ ነው። ስለዚህም በምንኖረው ኑሮ፣ በምንሰጠው አገልግሎት፣ በምንሳተፍበት የቅዱሳን ህብረት እንዲሁም ሃብታችን እና ጉልበታችን ሁሉ ሳይቀር ለአንድ የወንጌልን አላማ ልንቆም ጥሪው ተሰቶናል። እኛም

መዝሙራችን ‘‘እጅ ለጃችን ተያይዘን እየሩሳሌም እንገባልን’’ ብቻ ሳይሆን እጅ ለጃችን ተያይዘን ለወንጌል ስራ እንቆማለን የሚል እንዲሆን ይገባል፡፡

## ጥናት ሁለት
## የወንጌል ይዘት

**ዓላማ:** ወንጌል፣ በኃጢያት ከእግዚአብሔር ለተጣላው አለም ክርስቶስ እንደ ሞተና፥ እንደተነሳ እንዲሁም ዳግም ተመልሶ እንደሚመጣ የሚያብስር የእርቅ ዜና መሆኑን በመረዳት በግልጽነት እንድናበስረው ማበራታት።

**መግቢያ:**

ወንጌል ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ ሰዎች የሚሰጡት መልስ ተመሳሳይ አይደለም። ለአንዳንዱ ወንጌል ወንጌል የሃብት እና ደስታ ማካበቻ መንገድ ነው። ለሌሎች እንዲሁ አንደኛው የሃይማኖት አይነት እንደሆነ ያስባሉ። ሆኖም ግን ወንጌል ምንድን ነው ብለው ለሚጠይቁ ሁሉ፥ አማኞች ግልጽና ትክክለኛ ምላሽን መስጠት መቻል አለባቸው። ምንም እንኳ በተለያዩ ሰዎች እና ቤተ እምነቶች ዘንድ የተለያየ ትርጓሜ ቢሰጠውም መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለወንጌል ምንነት የሚናገርው አንድ እና ግልጽ ነገር ነው። በዛሬው ጥናታችንን ከአዲስ ኪዳን አንዳንድ ነጥቦችን በማንሳት ስለዚህ ስለ ወንጌል ምንነት መሰረታዊ እውነቶችን ለመጨበጥ እንሞክራለን።

ስለዚህ የዛሬው ጥናታችን “ወንጌል ምንድን ነው?” በሚለው አብይ ጥያቄ ላይ ያተኮረ ይሆናል። ወንጌል የሚለው ቃል ጥሬ ትርጉሙ “የምሥራች ቃል” “የደስታ ዜና” ማለት ነው። የምን ምስራች? ወይንም የምን ዜና? ብለን ብንጠይቅ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ወንጌል የምን ምስራችህ እንደሚያበስር በግልጽ ያስተምራል። ይህንን ምስራች ከዚህ በታችህ በተዘረዘሩት ነጥቦች እንመለከታለን።

### መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ወንጌል ምንነት ምን ይላል?

1. **ወንጌል ስለ ክርስቶስ የሚናገር ዜና ነው።**

በሮሜ 1፡ 3-5 እና በ1ኛ ቆሮ 15፡4 መሰረት ወንጌል የክርስቶስ ዜና መሆኑን እንረዳለን።

በሮሜ 1:4 መሰረት ወንጌል ክርስቶስ ኢየሱስ

- በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለመወለዱ
- እንደ ቅድስና መንፈስ ከሙታን ስለመነሳቱ
- በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለመገለጡ የሚናገር እውነት መሆኑን ሲነግረን

በ1 ቆሮ 15፡4 ይኸው ወንጌል የሚመሰክረለት ጌታ መጽሐፈ እንደሚል

- ስለ ኃጢያታችን መሞቱን
- መቀበሩን እንዲሁም
- በሦስተኛው ቀን ከሞት ስለመነሳቱ የሚያበስር ዜና ነው።

ስለዚህ በሮሜ 1:4 እና በ1 ቆሮ 15፡4 መሰረት ወንጌል በኃጢአት የጠፋውን የሰው ልጅ ለማዳን ክርስቶስ ኢየሱስ ሰው ሆኖ መምጣቱን ስለ ሰው ኃጢአት ዋጋ መሞቱን መቀበሩን እንዲሆም መነሳቱን፣ ወደፊት ደግሞ ተመልሶ የሚመጣ መሆኑን የሚያበስር ዜና ነው። ስለዚህም ወንጌል የምስራች እንጂ የሃዘን ቃል አይደለም። ወንጌልንም ሰምቶ ለሚቀበለው ብልህነት እንጂሞኝነት አይደለም።

2. **ወንጌል በሞት ጥላ እና ፍርሃት ለሚኖሩ ሕያው የሕይወት ተስፋ ነው።**

ወንጌልን የምስራች የሚያደርገው አይነተኛ ነጥብ በኃጢአት ለጠፋው እና ከሞት በቀር ተስፋ ለሌለው የሰው ዘር ሕይወት የሚገኝበትን መንገድ መስጠቱ ነው። ከአዳም ጀምሮ መላው የሰው ዘር በኃጢአት መጥፋቱ እና ለሞት መታጨቱ ግልጽ ነው (ሮሜ 5፡12-21)። ክርስቶስ ኢየሱስ ሰው ሊከፍለው የሚገባውን የሞት ዋጋ በመክፈሉ ዛሬ ለሚያምንበት ሁሉ የዘላለም ህይወት ተሰቶታል (ዮሐ 3፡16፣ 36፤ 5፡24)።

ስለዚህ ወንጌል የትንሳኤ ዜና ነው ማለት እንችላለን። ወንጌል የሚናገርለት ጌታ ራሱ "ትንሣኤና ሕይወት ነኝ!" ከማለቱም ሌላ "የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል" ሲል በክርስቶስ ለሚያምን ከሞትም በኃላ ትንሳዔ እንደሚሆንለት አስረድቷል (ዮሐ 11፡ 25, 26)።

### 3. ወንጌል በኃጢያት ለታወረ የሰው ልጅ የብርሃን ጮራ ነው።

ኃጢአት በሰው ልጅ ላይ ያመጣው ቀውስ በሞት ጥላ እና ፍርሃት እንዲኖሩ ከማድረግ ሌላ በጨለማ እንዲመላለስ ማድረጉ ነው። ስለዚህም ሰው በራሱ ጥረት የእግዚአብሔርን እውነት እና ብርሃን አጥርቶ ማየት አይችልም። ሰው በጨለማ ስለተያዘ እና ስለታወረ የእግዚአብሔር ነገር አይገባውም። እንዲያውም በኃጢያት ለጠፋው ሰው የእግዚአብሔር ነገር ሞኝነት ነው(2ኛ ቆር 4፡3-4፤ 1ኛ ቆር 1፡18 )። አሁን ግን ክርስቶስ ለሚያምንበት የአለም ብርሃን ሆኖ መጥቶአል። ". . . እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም" (ዮሐ 8፡12)።

### 4. በአዳም በደልል ምክንያት ከእግዚአብሔር ለራቀ ሰው የእርቅ መንገድ ነው።

ኃጢአት በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የሚለይ የጥል ግድግዳ ነው። ሰው በኃጢአት ከጠፋ ጀምሮኦ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል ትልቅ መለያየት ሆኗል። አሁን ኃጢአተኛውን ሰው ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርብ ክርስቶስ ሞቶአል (1ኛ ጴጥ 3፡18)። ስለዚህም ሰው ከ2ኛ ቆሮ 5፡19 እና ከ1ኛ ጢሞ 2፡5 እንደምንማረው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ በማመን እርቅ መፍጠር ይችላል።

- "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።" 2ኛ ቆሮ 5፡19፣
- መካከለኛ/ አስታራቂ "አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤" 1ኛ ጢሞ 2፡5

### 5. ወንጌል የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል ነው።

ብዙ ጊዜ ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር እንደሚያጣላ በመረዳት፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ወይንም ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ የተለያየ አማራጭ እንዳላቸው ያስባሉ። መጾም፣ መመጽወት፣ በብትሕውና መኖር ዘላቂ መፍትሔ ተደርገው በብዙዎች ዘንድ ይታመናሉ። ሆኖም ግን እነዚህ ሁሉ መልካም ነገር ቢሆኑም ሰውን ግን ወደ ድነት ለማምጣት ኃይል የላቸውም። አንደኛ እነዚህ ነገሮች በአማኙ ዘንድ የሕይወት ለውጥ ለማምጣት ጉልበት የላቸውም። ሁለተኛ ሰውን ከሞት ኃይል ነጥቆ ትንሳኤ የመስጠት ኃይል የላቸውም።

ወንጌል ግን ልዩ ነው! ጳውሎስ እንዳለው "በወንጌል አላፍርምና፣ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና"(ሮሜ 1፡16)። ወንጌል አማኙን በዚህ አለም ሲመላለስ ለእግዚአብሔር እንዲኖር ጉልበት ከመስጠቱ በላይ፣ ከኃጢአት እና ከሞት ነጥቆ ትንሳኤን ለሚሞተው ሰው መስጠት የሚችል ኃይል ነው።

### 6. ወንጌል የጌታን ወደ አብ ማረግ እንዲሁም ዳግም ምጻቱን የሚያውጅ ነው።

ወንጌል የጌታን ሞትና ትንሳኤ ብቻ ሳይሆን ዛሬ ስለ ኃጢአተኛው ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ይታይ ዘንድ ወደ አብ ማረጉን (ዕብ 9፡24) ኋላም ያመኑበትን ወደራሱ ሊሰበስብ እና በአለም ላይ ሊፈርድ ዳግም የሚመጣ መሆኑን የሚያስተምር ነው (ራዕይ 1፡6-9 ፣ 18 ፤ 22 ፡ 10-13)።

**7. ወንጌል ከክርስቶስ በስተቀር የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅ ሊፈጥርበት የሚችልበት መንገድ እንደሌለ የሚያስተምር ነው።**

እንግዲህ ከላይ እንዳየነው ወንጌል ስለ ክርስቶስ እና በእርሱም በኩል ስለሚገኝ ድነት የሚያስተምር ዜና ነው። ወንጌል በምንም አይነት መልኩ ስለ መላዕክት፣ ስለ ጻድቃን ሰማዕታት ወይንም በራስ ጥረት ስለሚገኝ ድነት አያስተምርም። መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ አፍ ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚናገረው ድነት የሚገኘው በክርስቶስ ብቻ እንደሆነ ነው። ‘‘መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና’’ ሐዋ 4፡12። ከዚህም ባሻገር የሚከተሉትን ጥቅሶች ልብ ብለው ያጥኗቸው ዮሐ 14፡6፣ 1ኛ ጢሞ 2፡5።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ወንጌልን እንዴት ነው የምትተረጉመው?
2. ወንጌል በሮሜ 1፡4 መሠረት ከጌታ ማንነት አንጻር እንዴት ነው የተገለጸው?
3. የወንጌልን ይዘት አስመልክቶ በ1ኛ ቆሮ. 15፡ 3-4 በግልጽ መነገር ያለባቸው ነጥቦች ምንድን ናቸው?
    - መዝ. 16፡10፤ ኢሳ 53ን ተመልከቱ]
4. በዮሐ. 1፡1-13 ክርስቶስ ከተገለጠበት ቃል አንጻር ወንጌል ምንድን ነው?
    - ወንጌል ብርሃን ነው ሲባል ምን ማለት ነው? ኢሳ 9፡1-7
5. ከክርስቶስ ማንነት የተነሳ በዮሐ 6፡ 35 ፣ 11፡25፣26 መሰረት ወንጌል ፧ ምን ያስከፈትልናል? እንዴትስ ብህያወታችንይገለጻል?
6. ከወንጌል የተነሳ ስለ ተገለጠ ተስፋና ፍርድ ከ 1 ዮሐ. 5፡10-12 ምን ትገነዘባለህ? በርግጠኝነት አንተ በየት ነህ?
7. በማስታረቅ አገልግሎት የክርስቶስ ሥራ ምንድን ነው? የአንተስ? በ 2 ቆሮ 5፡19 [1ጢሞ. 2፡5]
8. የመስቀሉ ቃል የሚባለው ምንድን ነው? ይህ ቃል በሰዎች መካከል ስለሚፈጥረው ልዩነት ተወያዩ። [1 ኛ ቆሮ. 1፡ 18-23]
9. የወንጌልን ተስፋ፥ ግርማና ፍጻሜን በተመለከተ አበይት መልዕክቱ ምንድ ነው ትላለህ? ለምን? [በሐዋ. 1፡9-11፤ ራዕይ 1፡6-9፣18፣ 22፡ 10-13 መሰረት]

***መደምደሚያ***

ወንጌል ስለ ክርስቶስ ገድል የሚናገር ዜና ነው። በኃጢአት የጠፋውን ሰው ለመፈለግ ሲል ክብሩን ሁሉ ትቶ ከሰማይ መውረዱን፣ እንደሰው ስጋ ለብሶ ስለ ኃጢአታችን መሞትና መቀበሩን፣ ሞትን አሸንፎ በትንሳኤ መነሳቱን፣ ዛሬ ሰለ ሰው ይታይ ዘንድ በአብ ዘንድ መቀመጡን ወደፊት ደግሞ የሚያምኑበትን ለመሰብሰብ እንዲሁም በአለም እና በሰይጣን ላይ ለመፍረድ ዳግም የሚመጣ መሆኑን የሚያወሳ ዜና ነው። እኛም ስንመሰክር እና ወንጌልን ለሌሎች ስናዳርስ የምንናገረው እወነት ይህንን ማዕከል ያደረገ እንዲሆን ይገባል።

## ጥናት ሦስት
## ወንጌልን የማሰራጫ ስልት

**ዓላማ፡-** በግል ሆነ በጋራ ጊዜያችንን፣ ችሎታችን ጊዜአችንንና ንብረታችንን ተጠቅመን ወንጌልን ልናሰራጭ የምንችልበትን ስልታዊ መንገዶች መጠቆም

**መግቢያ፡-**

ብዙ ጊዜ እንደሚመስለን ወንጌልን ይዞ ለመውጣት ያለው ብቸኛ አማራጭ በመንገድ ለምናገኘው ሰው መመስከር አይደለም። አማኝ በገባው እና በሚችለው መንገድ ሁሉ ወንጌልን ማዳረስ ይችላል። ሆኖም ግን እንደተሰጠን ጸጋ እና አቅም መጠን በወንጌል የምንደርስበት ቦታ፣ የምናበረክተው አስተዋጽኦ እኩል ላይሆን ይችላል። ሆኖም ግን ሁላችንም ወንጌልን ለማዳረስ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው ብዙ አማራጭ መንገዶች አሉ። ለምሳሌ በቅርብ ለሚያዩን በአኗኗራችን እና በአካሄዳችን በምንሰጠው የግል ህይወት ምስክርነት (personal evangelism)፥ በራሪ ወርቀቶችን (tract) በማሰራጨት፣ በመንገድ ላይ ለምናገኛቸው ሰዎች ስለ ጌታ በመንገር (street evangelism) መመስከር እንችላለን። ከዚህም ባሻገር ለወንጌል ጥሪ ያላቸው አገልጋዮች በታላላቅ የስብሰባ አዳራሾች ወንጌልን በመስበክ (mass evangelism) በአንድ ጊዜ ለብዙኃኖች ወንጌልን በማድረስ ወንጌልን የሚያሰራጩት ሌላኛው አማራጭ መንገድ ነው።

እንግዲህ ወንጌልን ማሮጥ የምንችልነት ብዙ አማራጭ ስላለን፣ አደራችንን ችል ሳንል ራሳችንን ለጌታ ስራ ታማኝ አድርገን ማቅረብ ይጠበቅብናል። ከላይ ከዘረዘርናቸው ወንጌልን በቀጥታ ለሰዎች ከምናደርስበት መንገዶ ባሻገር በወንጌል እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ መሆን የምንችልባቸው ሰፊ እድሎች አሉ። ለምሳሌ

- ለወንጌል ስርጭት እንዲረዳ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ፣
- በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት
- ላልዳኑት በመጸለይ
- ወንጌልን በማሰራጨት ለሚደክሙት በመጸለይ
- ወንጌልን ለሌላው ማድረስ የሚችሉ ደቀመዛሙርትን በማፍራት እንዲሁም
- ያላመኑት ወንጌል በሚሰበክበት ቦታ እንዲገኙ በመጋበዝ

በወንጌል ስርጭት ስራ ውስጥ መሳተፍ እንችላለን።

በወንጌል ስራ ውስጥ እጃችንን ልንዘረጋ የምንችልባቸው መንገዶች ብዙ ቢሆኑም ያላመነ ሰው ስናገኝ፣ ምን ብዬ ልጀምር? ምን ልናገር? እንዴት ነው ግለሰቡ ጌታ እንዲቀበል የምረዳው? … የሚሉት የብዙዎች ጥያቄ ነው። ለነዚህ ሁሉ አንድ አይነት መልስ ባይኖርም፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ነጥቦች ግን እጅጉኑ ሊረዱን ይችላሉ።

### 1. ከየት ቦታ እንጀምር?

ወንጌልን ለማዳረስ ከጌታ የተሰጠን ልዩ ጥሪ ከሌለን በስተቀር፣ ከሰፈር እና ከቀዬ ተፈናቅለን ሌላ አገር መሔድ አይጠበቅብንም። በሰፈር፣ በስራ ቦታ፣ በትምህርት ገበታ … በተለያየ ገጠመኝ ከምናገኛቸው እና አጠገባችን ካሉ ሰዎች መጀመር እንችላለን። የስራው ስፋት እና የጌታ ጥሪው ሲያስገድድ ደግሞ ራቅ ወዳለው ቦታ መሔድ ይቻላል። በሐዋ 1፡8 ላይም ጌታ ለሐዋሪያቱ ያስተማራቸው መንገድ ይህንኑ ነበር፤ ከኢየሩሳሌም እንዲጀምሩ ከዚያም አልፈው አለምን እንዲደርሱ።

ስለዚህ ከየት ልጀምር ለሚለው ራሳችንን ልንጠይቅ የሚገባው በአጠገቤ ማን አለ ጌታንስ ያውቃል ወይ የሚል ነው። በቅርብ የምናውቃቸው በጌታ እንዳይደሉ ከተረዳን ሥፍራቸው ተገኝተን በሚገባን እና በሚቀለን መንገድ ሁሉ ጌታን ልናሳይ እንችላለን። ሆኖም ግን ምንም በቅርብ የምናውቃቸው ሰዎች ቢሆኑም ወደ ሰዎቹ መሄድ እና ወንጌልን ለማድረስ እርምጃውን መውሰድ ያለብን እኛ ነን። ለዚህ ጌታ በዮሐ 4 ላይ በራሱ አነሳሽነት ያነጋገራትን ሴት ስናይ፣ ፊሊጶስ ኢትዮጵያዊውን

ጃንደረባ እናዳነጋገረው እንዲሁም ጴጥሮስ የመቶ አለቃ ቆርኖሊዎን የቀረበበትን መንገድ ስናይ እኛም ወንጌልን ለማድረስ የመጀመሪያውን እርምጃ መውሰድ ያለብን እኛ እንደሆንን እንረዳለን።

## 2. እንዴት ልጀምር?

ስለ ጌታ መመስከር እየፈለግን ግን እንዴት ልጀምር ብለን ግራ መጋባታችን የብዙኋኖቻችን ችግር ነው። ሆኖም ግን ገና ልንመሰክርለት የምንፈልገውን ሰው ገና ስናገኘው፣ "አንተ ኃጢአተኛ ነህና  ንስሃ ግባ!" ማለቱ ብዙ የሚያስኬድ አይደለም። ሆኖም የጋራ ጉዳይ እና ፍላጎት አንስተን በጥንቃቄ ወደ ምስክርነት መሄድ ተመራጭ መንገድ ነው። ለዚህ ጌታ ኢየሱስ በዮሐ 4 ላይ ውሃ ልትቀዳ የመጣችውን ሴት ያነጋገረበት መንገድ ጥሩ ምሳሌአችን ነው።

- የውኃ ጥም ለሴቲቱም ለጌታ የጋራ ነገራቸው ነበር።
- የጋራ ዕውቀትን ከአብይ ጉዳይ ጋር ማዛመድ። (አባታችን ያዕቆብ. . .)
- ምድራዊ ሁኔታን ከመንፈሳዊ እውነት ጋር ማያያዝ

## 3. ቃሉ መስተዋት ሆኑ የሰውን ሁኔታ እንዲያሳይ አድርግ

ምንም እንኳ ለንግግር መክፈቻ እና መንደርደሪያ ከጋር ጉዳዮችን መንሳት መልካም ቢሆንም፣ የምናስተላልፈው ዋነኛው ቃል ግን የእግዚአብሔር ቃል ነው። በዚህ ቃል ነው ሰዎች ራሳቸውን ማየት እና ስለራሳቸው ትክክለኛ ግንዛቤ ሊኖራቸው የሚችለው።

- ❖ ከኢየሱስ ጋር የሚነጋገርና የጌታን ቃል የሚያደምጥ ማንነቱን ሳያይ አይቀርም። የሰውን የውስጥ ሁኔታ መረዳት የሚችል ጌታ የልብን ይናገራልና። ዮሐ 4:13-19
- ❖ ከኃጢአት የተነሳ ፍርድ አለ። ሮሜ 3:23; 5:12; 6:23, ሕዝ. 18:20, ማቴ5:19-20
- ❖ ከጌታ የተነሳ ሕይወት ተሰጥቶናል። ሮሜ 3:23-24; 5: 19-21; 6:23,

## 4. ፍቅሩንና ፍርዱን በሚዛናዊ መንገድ መናገርህን አትዘንጋ

በወንጌል አገልግሎት ውስጥ ክርስቶስን ለሞት እስከመስጠት ድረስ ሰውን መውደዱን መናገር አይነተኛ ነጥብ ቢሆንም፣ እግዚአብሄር አፍቃሪ እንደመሆኑ መጠን ደግሞ እንደሚፈርድ ማሳሰብ የወንጌሉ ሌላኛው ነጥብ መሆኑን ማንሳት መዘንጋት አይገባም። እግዚአብሔር ስለ ፍቅሩ ክርስቶስን እንደሰጠ፣ ክርስቶስን ለሚገፉ ደግሞ እግዚአብሔር የገሃነምን ፍርድ ይሰጣል (ሕዝ. 18:20, 23, 32, ማቴ. 11፡28)።

## 5. የምትናገረው ወንጌል የሚያድን እና የሚለውጥ መሆኑን አትዘንጋ

አቀራርብህ የሚስብ መሆኑ አስፈላጊ ጉዳይ ቢሆንም የያዝከው መልዕክት ከሁኔታዎችና ከማንነት በላይ መሆኑን አትዘንጋ። ካለፈው ጥናታችን እንዳየነው ወንጌል የሚያድን የእግዚአብሔር ኃይል ነው ሮሜ 1፡16-17።  ስለዚህም በምንናገረው ወንጌል እግዚአብሔር በጨለማ ላሉ ብርሃንን፣ ተስፋ ለሌላቸው ተስፋን እንደሚያወጣ እያወቅን በድፍረት ልንናገረው እንጂ በፍርሃት እና በመሸማቀቅ ሊሆን አይገባም (2ኛ ጢሞ 1፡10-11)።

## 6. የምትመሰክርላቸው እንዲወስኑ እና ንስሃ እንዲገቡ እድል ስጣቸው

በወንጌል ምስክርነት ውስጥ ትልቁ ቁም ነገር መናገር ብቻ ሳይሆን ሰዎች እውነትን ከሰሙ በኋላ ውሳኔ እንዲወስኑ መርዳት ነው። ወንጌልን ከሰሙ በኋላ አሁንም ጌታን ለመከተል ፈቃደኛ ካልሆኑ ወደፊት የሚመጣ ፍርድ እንዳለ አሳስቦ መተው ይቻላል። ሆኖም ግን የጌታን መንገድ ለመከተል ከመረጡ ንስሃ ገብተው፣ ሕይወታቸውን ለጌታ ሰጥተው አዲስ መንገድ እንዲጀምሩ ማገዝ ተገቢ ነው። እነዚህን ክፍሎች ያጢኗቸው ዮሐ.3:3,7; 5:39; 6:66-68; 12:42,43: 16:7-11 ሮሜ 10:10,11 ቲቶ3:5 ማቴ. 10:37, 38።

ሆኖም ግን የወንጌል ስርጭት ፍጻሜው ሰዎችን ወደ ጌታ ማምጣት ላይ ብቻ ሳይሆን የዳኑትን ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው (ማቴ 28፡19)። በመሆኑም ጌታን ለመከተል ሰዎች ከወሰኑ በኋላ በሕይወታቸው እንዲበረቱ እና ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ ወደ ቤተክርስቲያን ሕብረት ማምጣት እጅግ አስፈላጊ ነው።

**የውይይት ጥያቄዎች**

1. በሐዋ 1:8 መሰረት ሥፍራን በተመለከት ምን ትዕዛዝ ነው የተሰጠን? ይህ ከእኛ ጋር እንዴት ነው የሚያያዘው?
2. ከዮሐ. 4:7-13 ጌታ ሳምራዊቷን ሴት ወደ እውነት ለመመለስ ምን ስልትን ተጠቀመ?
   - የጋራ ነገር
   - ጊዜ
   - የታወቀ ዕውነት ላይ መመርኮዝ
   - ጉድለትና ምስራች
3. የመልዕክታችን መሠረት፥ መስታወት እና ብርሃን ምንድን ነው? ይህ
   - የሰውን ልብ ስረዳትና የልብን ስለመናገር ምን ኃይል አለው? **ዮሐ 4:13-19**
   - ኃጢአትን አስመልክቶ ልናስተላልፍ ስለሚገባን ሀቅ ምን ያስተምረናል? በሚከተሉት ጥቅሶች መሰረት ተመልከቱት ሮሜ 3:23; 5:12; 6:23, ሕዝ. 18:20, ማቴ5:19-20።
   - ምንስ ተስፋ ይሰጠናል?ከጌታ የተነሳ ሕይወት ተሰጥቶናል። ሮሜ 3:23-24; 5: 19-21; 6:23,
4. ሚዛን ጠብቅን ልንናገር የሚገባ እውነት ከሕዝቅኤልና ከሌሎች የመጸሐፍ ክፍሎች ምንድን ነው? ሕዝ. 18:20, 23, 32, ማቴ. 11፡28
5. መልዕክትህ የመታደግ ኃይል እንዳለው የምትደገፍበት ነገር ምንድን ነው? ለሰሚዎችስ የምትሰጠው የጸና መልዕክት ምንድን ነው? ኢሳ: 53: 1-12፤ 2ቆሮ.5: 15፤ ገላ 2:1, 8-9 ሮሜ፡8:1
6. ምስክርነት ሙሉ እንዲሆን እውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ማገዝና ማበረታትህን አትዘንጋ።
   - ጌታ ኢየሱስ ሰዎች ምን አይነት ውሳኔን እንዲያደርጉ እና እንዴት ነበር የሚገፋፋቸው?ስለ ውሳኔ ቁርጠኛነት፤ ዮሐ.3:3,7; 5:39; 6:66-68
   - ስለንስሃና ፍሬው ከዮሐ16:7-11 እና ቲቶ3:5 ምን ትረዳለህ?
   - ውሳኔ ጽኑ ምርጫ መሆኑን ከሚከተሉት ክፍሎች ምን ትረዳለህ? እንዴትስ ነው ልታዘጋጃቸው የሚገባህ?ዮሐ12:42,43
   - ከሮሜ 10:10,11 ማቴ. 10:37, 38 ቆርጦ ለጌታ ስለመለየት ልናስታውቃቸ የሚገባን እውነት ምንድን ነው?
7. መመስከር ብቻ ሳይሆን በጋራ የዳኑትን ለመያዝ መጸሐፍ ልናደርግ ስለሚገባን ነገር ምን ይላል? 1ቆሮ.3:6፣7
8. በዚህ ሊኖርህ ስለሚገባው ድርሻ የምትረዳውንና ያለህን ጸጋ ለቡድንህ አካፍል።

**መደምደሚያ፡-**

ወንጌልን ለሌሎች የምናደርስበት መንገዱ ሰፊ እና ብዙ ነው። የወንጌል ስርጭት ሁላችንም ልንሳተፍበት የምንችልበት የስራ መስክ ነው። በመሆኑም እድሉን ስናገኝ በማስተዋል ቃሉን በመናገር፣ በሌላው ጊዜ ደግሞ አቅማችን፣ ጊዜአችን እና ችሎታችን በሚፈቅድው ሁሉ በተከፈተልን መንገድ ሁሉ ልንሳተፍ ይገባል።

**ጥናት አራት**
**ተግዳሮትን የሚቋቋም ወንጌል**

**ዓላማ**: የአማኞች መያያዝ ተግዳሮትን ድል ነስቶ ወንጌል እንዲወጣ  አስፈላጊ መሆኑን ማስገንዘብ።

**መግቢያ**

ቀጣይነት ያለውን የወንጌል አደራን ለመግለጥ፥ "የእያንዳንዱ አማኝ ህይወት የሐዋርያት ሥራ ሃያ ዘጠነኛው ምዕራፍ ነው" ይባላል። የዚህ አባባል እውንነት በየግላችን እና በኅብረት ስለወንጌል ባለን መረዳት እና መሰጠት ላይ የተወሰነ ነው።
የቅዱሳን አንድነት ዓለምን በወንጌል በተቀላጠፈ መንገድ እንድንደርስና ውጤታማ እንድንሆን ያደርገናል። የመጀመሪያዪቱ ቤተክርስትያን በጌታ እገዛ እንዴት ነበር ያሰራጨችው? ይህን አስመልክቶ ከሐዋሪያት ሥራ አንዳንድ ነጥቦችን ለማጤን እንሞክራለን።
በሐዋሪያት ዘመን በመያያዝ ያላቸው ትጋት ወንጌልን በአጭር ጊዜው ውስጥ እጅግ እንዲበዛ አድርጎታል። ጌታ ካረገ በኋላ ሐዋሪያት እና ደቀመዛሙርት የወንጌልን አደራ ከጌታ ተረክበዋል (ማቴ 29፡18-21) ። ሆኖም ይህን አደራ ወደ ፍጻሜ ማድረስ ግን ቀላል አልነበረም። ይገጥማችተ የነበረውን ፈተና እና ተግዳሮት ተቋቁመው አርባ እና ሃምሳ ባልሞላ አመት ውስጥ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ወጥቶ በአለም ዙሪያ መሰራጨት ችሏል። ይህ እንዴ ሊሆን ቻለ ብለን ብንመረምር፣ አንደኛው ምክኒያት የቅዱሳኑ በአንድ ልብ መያያዝ ነው። ተያይዞ ወንጌልን ማብሰር እና ዋጋን እየከፈሉ ነፍሳትን መድረስ ህይወታቸው እንደነበረ በግልጽ እናያለን። በዛሬው ጥናታችን ከሐዋሪያት ዘመን በወንጌል ስርጭት ውስጥ ስለሚኖሩ ተግዳሮቶች እና የቅዱሳን መያያዝ እንዴት ተግዳሮቶችን አሸንፎ ወንጌልን ለማዳረስ እንደሚረዳ እንመለከታለን።

**ተግዳሮቶች**

ጌታ ወደ አብ ሊያርግ ባለበት ሰአታት ለሐዋሪያቱ ወንጌልን በመጀመሪያ በኢየሩሳሌም፣ ከዚያም በይሁዳ ብሎም በሰማሪያ እናም እስከ ምድር ዳር ድረስ ወንጌልን እንደሚያዳርሱ ተናግሮ ነበር (ሐዋ 1፡8)። በእርግጥም የሐዋሪት ሥራ መጽሐፍን እና ሌሎች የአዲስ ኪዳን መጽሐፍትን ስናይ በጥቂት አመታት ውስጥ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ወጥቶ በአለም ዙሪያ ተዳርሷል። ይህ ሲባል ነገሩ አልጋ በአልጋ ሆኖ በቀላሉ የተሳካ ቢመስልም፣ እውነታው ግን ወንጌል እጅግ ፈታኝ በሆኑ ተግዳሮቶች ውስጥ አልፎ ነው የተሰራጨው። በጊዜው ከነበሩት እና ዛሬም እኛ ሊታገሉን ከሚችሉት ተግዳሮቶች ጥቂቱን ለምሳሌ መጥቀስ እንችላለን።

## 1. ስደት እና መከራ

በወንጌል ስርጨት ውስጥ መከራ አይነተኛው ተግዳሮት ነው። የወንጌሉ ራስ የሆነው ክርስቶስ ራሱ እስከ መስቀል ሞት ድረስ መከራ ተቀብሏል። ከዚያም ሐዋሪያቱ ወንጌልን በሚያደርሱበት ጊዜ ሁሉ መከራ እንደ ጥላ አብሯቸው የሚጓዝ ነገር ነበር። የሐዋ 5: 17-21, 6:1-2, 7:59-60, 8:1-3 12:1-5 እንደ ዋቤ መጥቀስ ይቻላል። ከዚህም በላይ ሐዋሪያቱ በሙሉ ሕይወታቸው ያለፈው ለወንጌል መከራን ሲቀበሉ ነው። ሆንም ግን መከራ የወንጌል ስርጭትን ሊያቆም አልቻለም። ዛሬም ይኸው ፈተና በተለያየ መልክ እና ሁኔታ በዘመናችን ለወንጌል እንቅፋት ሲሆን ይገኛል።

## 2. ክፍፍል እና መለያየት

በአንድ ልብ እና አሳብ እንዲኖሩ እና እንዲሰሩ አማኞች ጥሪ ቢኖራቸውም፣ መለያየት፣ መጋጨት እና መከፋፍል ቤተ ክርስቲያን ገና ከጠዋቱ ይገጥማት የነበረ ችግር ነው (ሐዋ 6፡1፣ 1ኛ ቆሮ 1፡10-12)። መለያየት፣

አማኞች ሳይታሰብ አይናቸውን ከወንጌል ስርጭት ላይ እንዲያነሱ የሚያደርግ መርዝ ቢሆንም ቅሉ፣ ግን የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን አማኞች ወንጌልን በተገቢ ሁኔታ ለማዳረስ ችለዋል።

**3. የሀሰት ትምህርቶች**

ሌላው አስቸጋሪ ነገር ደቀመዛሙርት እውነተኛውን ወንጌል ሲሰብኩ፣ የሰበኩትን የሚመርዝ የሃሰት ትምህርት ተከትሎ መግባቱ ነው። መዳን በክርስቶስ ብቻ ነው ሲሉ፣ የለም መዳን በክርስቶስ በማመን እና ሌሎች ስርዓቶችንም በመጠበቅ ነው የሚሉ እና የብዙዎችን ልብ የሚያታልሉ መናፍቃን  በየጊዜው እና በየቦታው እየገቡ ፈተና ሆነውባቸዋል (ሐዋ 15፡1-2)። ይህም ፈተና ግን ሐዋሪያትን ወንጌል ከማሰራጨት አልገደባቸውም።

**4. የተለያዩ የእምነት እና የባህል ተጽዕኖዎች**

ሐዋሪያት ከኢየሩሳሌ እየወጡ ወደ ሌላ ቦታዎች በሄዱ ቁጥር አዳዲስ እምነት እና ባሕል ማየታቸው የተለመደ ቢሆንም፣ ላልተለመዱ እምነቶች እና ባሕል ወንጌልን ማስተዋወቅ ቀላል አይደለም። በተለምዶ ከቀድሞ ጀምሮ የያዙትን እምነት እና ባሕል መልቀቅ ቀላል አይደለም። የሐዋ 10፡1-16 ያለውን ስንመለከት እንኳን ወንጌል ላልደረሳቸው ሰዎች እንደ ሐዋሪያው ጴጥሮስ ላለው ታላቅ ሰው እንኳ የነበረውን የብሉይ ኪዳን አስተሳሰብ ለመልቀቅ ከብዶት እንደነበር እናያለን። ሐዋሪያት ለወንጌል አገልግሎት ሲሄዱ፣ የሚደርሱበት ቦታ መጽሐፍ ቅዱስን በጥቂቱ የሚያውቁ፣ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ዘንድ ሳይሆን ፈጽሞ እግዚአብሔን የማያውቁ ጣኦት አምላኪዎች የተለየ እምነት እና ባሕል ያላቸው ሰዎች ዘንድ ነው (ለምሳሌ ሐዋ 17፡16 - 34)። ከዚህም ባሻገር፣ ወንጌል ሲሰበክላቸው እምነታቸውን እና ባሕላቸውን ለማጥፋት ሆን ተብሎ የመጣ መጤ ትምህርት እየመሰላቸው ረብሻ የሚፈጥሩ አልጠፉም( ሐዋ 17፡1-9፤ 19፡23-41)።

ከላይ የዘረዘርናቸው ነጥቦች ከብዙ ጥቂቶቹ ቢሆኑም ወንጌልን ለማዳረስ የሚገጥሙን ተግዳሮቶች በቁጥር ትንሽ አይባሉም። ሆኖም ግን በእነዚህ ሁሉ ትግል ውስጥ አልፎ የመጀመሪያው ዘመን ቤተክርስቲያን በተሳካ መልኩ ወንጌልን እንዴት ልታዳርስ ቻለች ብንል፣ አንደኛው ምክኒያት ቅዱሳን ተያይዘው በአንድ ልብ መስራታቸው ነው።

ገና ከጠዋቱ በአንድ ልብ እና አሳብ ሆነው አብረው ነበሩ( ሐዋ 2፡43-47፣ 4፡32)። ጥያቄ ወይንም ጉዳይ ሲኖራቸው በልብ አንድነት ተያይዘው ይጸልዩ ነበር (ሐዋ 1፡14፣ 24-25፣ 2፡42)። አንደኛው ወገን ስለ ጌታ ሲታሰር ወይንም መከራ ሲቀበል በሕብረት ተያይዘው ይጸልዩ ነበር (ሐው 12፡ 1-17) በወንጌል ምክኒያት ለሚታሰረው እና ለሚቸገረው ሌሎቹ የሚያስፈልገውን ይልኩ ነበር (ፊል 4፡10-17፤ ዕብ 10፡34)። የሃሰት ትምህርት ሲነሳ በአንድ ልብ ያወግዙት ነበር (ሐዋ 15)። ባጭሩ ወንጌል መሮጥ እንዲችል ሁላቸውም በመያያዝ እና በአንድነት ይሰሩ ነበር አንድነት ሲኖር በሕብረት ተርዳሮትን መቋቋም ስለሚቻል። ስለዚህም ነው ጳውሎስ በተለያየ አጋጣሚ አማኞች በአንድ ልብ እንዲሆኑ እና እንዲያያዙ ደጋግሞ ማሳሰብ ያስፈለገው (1ኛ ቆሮ 1፡10፣ ፊል 4፡2)። ጌታም ወደ መስቀል ከመውርዱ በፊት ለደቀመዛሙርቱ የጸለየላቸው እና ይናፍቅላቸው የነበረ አንድነትን እንደነበረ እናስታውስ (ዮሐ 17፡20-23)።

***መደምደሚያ***

በዚህ አለም ወንጌልን የሚያዳፍኑ ብዙ ተግዳሮቶች አሉ። ሆኖም ግን በግል ነጠላ ሆኖ ተግዳሮትን ማሸነፍ ከባድ ከመሆኑም በላይ በነጠላ መታገል ለዲያቢሎስ ወጥመድ ሊያጋልጥ ይችላል። ተያይዞ በሕብረት መቆም ግን ራስን ከዲያቢሎስ ሽንገላ ከማስጣል ባሻገር፣ ተግዳሮቶችን ሁሉ አሸንፎ ወንጌልን ለማዳረስ ትልቅ ዕድል ይሰጣል።

በመሆኑም አማኞች ሁልጊዜ ስለ ወንጌል በአንድ ልብ ልንጸልይ፣ ልንረዳዳ፣ ልንተሳሰብ፣ መወገዝ የሚገባውንም በአንድ ልብ ልናወግዝ ይገባናል።

***የመወያያ ጥያቄዎች፡***

1. በሐዋ 2:43-47 4:32, ስለ አዲስኪዳን አማኞች ኅብረት፥ ከጌታ ሥራና ከአማኞች መስጠት አንጻር የተገለጸው ምንድን ነው? ከዚህ ልንወስደው የምንችለው ትምህርት ምንድን ነው?

2. የወንጌል ሥራቸው ላይ የነበረባቸው ተግዳሮት ምን ነበር? ሐዋ 5: 17-21, 6:1-2, 7:59-60, 8:1-3 12:1-5
3. በነዚሁ ክፍሎች የቅዱሳኑ ምላሽ ምን ነበር? ከዚህ ምን ትማራለህ?
   - ለጌታ የሚገባውን አገልግሎት በአንድነት በመያያዝ ሁሉን በፍርጅ ፈርጁ ማድረግ
     - የበጎ አድራጎት ሥራና የወንጌልን ጉዳይ አንዱ ለሌላው እንቅፋት እንዳይሆን መትጋት
     - በጸሎትና በመንፈስ አንድነት ሁሉን በሥርአት ማድረግ
4. ቀድሞ የነበሩበት ባህልና እምነት በወንጌል ስርጭታቸው ላይ ምን አይነት ተጽኖ ነበረው? (ሐዋ. 10) ይህን መሰል ችግር ባይኖረንም በመሃከላችን ችግር ሊፈጥር የሚችል ምን ልምምድ ይኖረናል ትላለህ?
5. በዮሐ 4:35 (ማቴ 9:37፣ ሉቃስ 10:2) እና ሐዋ 8:26-40፡10 ላይ በመርኮዝ
   - ስለ ወንጌል አገልግሎት ባላደራና ስለ ወንጌል መስክ ምን ትገነዘባለህ?
   - የመንፈስ ቅዱስ ድርሻና የእኛ ዝግጁነትን እንዴት ትመለከታለህ?

   የሚከተሉትን ልብ በሉ
     - ከፊሊጶስና ጃንደረባው
     - ከጲጥሮስና ቆርኔሌዎስ
6. በሐዋ 8:19-24 ላይ የተገለጥ ተግዳሮትና የሐዋሪያት ምላሽ ምን ነበር? ወንጌሉን ለሚሰሙ ልንጠነቀቅላቸውን ልብ ልንለው ስለሚገባን ነገር ምን ያሳስበናል?
7. በወንጌል የሚደረሱት ነፍሳትን ማንነትና ባህርይ ስትመለከት ስለ ላኪው ጌታና ስለ ወንጌል ኃይል ምን ያስገነዝብሃል? (ምሳሌ፡- ጃንደረባው፥ ቆርኔሌዎስ፤ ሳውል እና ሲሞን)
8. በማንኛውም አይነት ተግዳሮት ውስጥ ሁሉ የመልዕክታቸው ማዕከላዊ ሀሳብ ምን ነበረ? ጽናታቸውስ? ሐዋ. 4፡8,31 5:27-32 10:38-43

   - የሰቀላችሁት፤ እግዚአብሔር ከሙታን ያስነሳው
   - የሙታን ትንሳኤጢአት
   - የኃጢአት ሥርየት

***መደምደምያ***

ወንጌል ያለዋጋ አልመጣልንም። አሁንም ያለዋጋ ልናስራጨው አንችልም። የግል ህይወታችን፤ በዙሪያችን ያለው ነገርና ሰይጣን ወንጌልን በቀላሉ እንዳናሰራጭ እንቅፋት ይሆኑብናል። ሁኔታው ምንም ከባድ ቢሆንም የጠራን ጌታና ወንጌሉ ብርቱ ስለሆነ በአላማችን ጸንተን እንገዝ።